በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አመሰራረት 1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ..3

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ..3

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 4

ክፍል ሁለት 5

ግኝቶች 5

2.1 ከቆጣሪ አሰጣጥ እስከ ቢል አሰባሰብ ድረስ ያለው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤..5

አዲስ ኃይል ፈላጊ ደንበኞች በቅደም ተከተላቸው መሰረት እየተስተናገዱ መሆኑን በተመለከተ፣..5

የደንበኞች መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣..6

ደንበኞች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን በተመለከተ፣..8

ለደንበኞች የሚሰጠው የትራንስፎርመር ተከላ እና ማሻሻያ አገልግሎት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ /በስታንደርዱ/ መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣..16

በቆጣሪ ንባብ ባለሙያነት ለተሰማሩ የድርጅቱ ሠራተኞች..18

የስራ መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ፣..18

አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኙ ደንበኞች ወደ ክፍያ..20

ስርዓት እንዲገቡ ማድረግን በተመለከተ፣..20

አገልግሎቱ ለሰጠው አገልግሎት በወቅቱ ክፍያ መሰብሰቡን በተመለከተ..22

የታሪፍ ለውጥ ሊደረግባቸው የሚገቡ ደንበኞችን በወቅቱ በመለየት የታሪፍ ለውጥ መደረጉን በተመለከተ..26

ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች የቤት ለቤት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን በተመለከተ..28

ክፍያቸውን በአግባቡ በማይፈጽሙ ደንበኞች ላይ..30

ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ፣..30

የኃይል ብክነት ለመቆጣጠር የተዘረጋው ስርዓትን በተመለከተ..33

የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ስርዓት ስለመዘርጋቱ በተመለከተ..35

የደንበኞች መብትና ግዴታን በተመለከተ አሰራሮች ሲሻሻሉ ድርጅቱ ለደንበኞቹ የሚያሳውቅ መሆኑን በተመለከተ..37

የተገልጋዮች እርካታ የዳሰሳ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ’..39

በውስጥ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ድርጅቱ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ 41
2.2 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኤሌክትሪክ ማከፋፊያ መስመሮች ብልሽት ቅድመ መከላከልና ድህረ ጥገና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣ 43
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችና የትራንስፎርመሮች ላይ የቅድመ ብልሽት ጥገና ስራዎችን ማከናወኑን በተመለከተ፣ 43
የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች ላይ የማሻሻያ ስራ መሰራቱን በተመለከተ 49
በከተሞችና በገጠር የኃይል ማሰራጫ መስመር ሲበጠስ የኃይል አቅርቦቱ በተቀመጠው የጊዜ ተመን/ስታንደርድ/ መሰረት እንዲቀጥል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ' 53
ያለ ፕሮግራም የኃይል መቆራረጥን በሚዲያ ቀደም ብሎ ማሳወቅን በተመለከተ .. 55
የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ደንበኞችን በተቀመጠው ስታንደርድ ማስተናገዱን በተመለከተ 56
የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል በመረጃ ኔትወርክ መተሳሰርን በተመለከተ 59
ተቋሙ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ 60
2.3 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞችን ለማርካት ከውጭ (ከከተማ አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፓሬሽን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻአካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የዘረጋውየአሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማመሆኑን ማረጋገጥ፣ 62
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ስለመፈራረሙ በተመለከተ 62
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከደንበኞች ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ ስለመኖሩ በተመለከተ 64

ክፍል ሦስት 66

የመደምደሚያ ሀሳብ (CONCLUSION) 66
3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው 66
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው 67

ክፍል አራት 71

የማሻሻያ ሀሳቦች (RECOMMENDATION) 71

ክፍል አንድ

መግቢያ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አመሰራረት

1. ለሀገራችን የኢኮኖሚያና ማህበራዊ እድገት የኤሌክትሪክ ኃይል ድርሻ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል ከየትኛውም የመሰረተ ልማት አንፃር ሲታይ ወሳኝና መሰረታዊ በመሆኑ፣ በዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ ቀዳማይ ቦታ የሚይዝ የመሰረት ልማት ዘርፍ ነው፡፡

2. በሀገራችን የኤሌክትሪክ ብርሃን የተጀመሪው በ1890 ዓ.ም በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት የጀርመን መንግስት ለአፄ ሚኒሊክ ባበረከተው ጀኔሬተር አማካኝነት ሲሆን፣ ይህም ለቤተመንግስቱ ብቻ የሚያገለግል ነበር፡፡ ነገር ግን ኤሌክትሪክ በቤተመንግስቱ ብቻ ተወስኖ የነበረው ቀስ በቀስ ከቤተመንግስቱ መውጣት ጀመረ፡፡

3. አፄ ሚኒሊክ የመብራትን ጠቀሜታ በማየት አንዳንድ አቅም ያላቸው ነዋሪዎች ከ1920 ዓ.ም. ጀምሮ መግዛት ጀመሩ፤ በ1928 ዓ.ም. ጣሊያን የኢትዮጵያን በመውረሯ አዲስ አበባንና ሌሎች ጣሊያን በተቆጣጠረባቸው ከተሞች ዲዝል ተከለ፤ በነዚህም ጊዜያት ውስጥ በናዝሬት፣ በድሬዳዋ፤ በበደሌ፤ በሀረር፤ በጎንደርና በጅማ ከተሞች ጀኔሬተሮች ተተክለው አገልግሎት መስጠት ጀምረው ነበር፡፡

4. በ1952 ዓ.ም ሚኒሊክ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የቆቃ ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል በአቃቂ ወንዝ ላይ ገነቡ፡፡ ይህም በአዲስ አበባ የሚገኙትን አነስተኛ ፋብሪካዎችን እንዲያንቀሣቅስ ታቅዶ ነበር፡፡ ቀጥሎም መብራት ለቤተመንግስቱ እና ለኢንዱስትሪ ከመሆን አልፎ ወደ ህዝብ ቦታዎችና በቤተመንግስቱ አካባቢ ወዳሉ መንገዶች መዛመት ጀመረ፡፡

5. በሀገራችን መብራት አገልግሎት ወጥነው ባለው ተቋማዊ ይዘት ተላብሶ 1940 ዓ.ም በሸዋ መብራት ኃይል እና በከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች አስተዳደር የቆየው የኤሌክትሪክ ኃይል የማቋቋም፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል እና የመሸጥ ስራን እንዲያከናውን ታስቦ ጥር 21 ቀን 1948 ዓ.ም. በወጣው የመንግስት ማስታወቂያ ቁጥር 213/1948 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለስልጣን በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡

6. ከ1966 ዓ.ም አብዮት በኃላ ተመሳሳይ የስራ ባህርይ ያላቸው ድርጅቶች በአንድ ሚኒስቴር መ/ቤት ስር ተጠቃለው እንዲተዳደሩ ሲደረግ፣ ነሐሴ 20 ቀን 1969 ዓ.ም. የሚኒስትሮችን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 127/1969 ዓ.ም በማዕድን፣ ኃይል ማመንጫና የውሃ ልማት ሚኒስቴር ስር እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ሲሆን፣ ጥቅምት 8 ቀን 1974 ዓ.ም. የሚኒስትሮችን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 216/1974 ዓ.ም. ደግሞ የማዕድን ኃይል ምንጭ ሚኒስቴር ተብሎ ይጠራ በነበረው መ/ቤት ስር እንዲተዳደር ተደረጎል፡፡ ከዚያም መስከረም 6 ቀን 1980 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መስተዳደር ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/1980 የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተብሎ በተመሰረተው መ/ቤት ስር እንዲሆን ተደረጎል፡፡

7. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከተቋቋመ በኃላ በሰኔ 30 ቀን 1989 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፓሬሽን (ኢ.ኤ.ኃ.ኮ) የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

8. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 26(2) የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተብሎ በተመሰረተው መስሪያ ቤት ስር እንዲሆን ተደረጓል፡፡

9. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 303/2006 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፓሬሽን መንግስት ለአቅም ግንባታ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ተቋሙ ሁለት እራሳቸውን የቻሉ የልማት ድርጅት የተከፈለ ሲሆን፣ እንርሱም፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት ናቸው፡፡

10. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመላው ሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል በፍታዊነት ለሁሉም ዜጋ እንዲዳረስ ለማድረግ፤ ለነባር ደንበኞች አስተማማኝና ደረጃውን የጠበቀ ኃይል ለማቅረብ፤ ለአዳዲስ ደንበኞች የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያቀርብ የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው፡፡

11. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያከናውናቸው ተግባራት የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችን የግንባታና የጥገና ስራዎችና ማከናወን፣ እንደአስፈላጊነቱ የማከፋፈያ መስመሮችን ግንባታ በሥራ ተቋራጭ ማሰራት፣ የኤሌክትሪክ ሃይል

የማከፋፈያ መስመሮችን ማስተዳደር እና ጅምላ የኤሌክትሪክ ሓይል ገዝቶ ለደንበኞች የኤሌክትሪክ ሓይል አገልግሎት ሽያጭ ሥራዎችን ማከናወን፣ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና በፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም እንዲሁም ሪጅንና ማዕከላትን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

12. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2008/2009 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በመለየትና በማጣራት ችግሮቹ እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም ለመገምገም ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

13. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ በአገልግሎቱ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2011 ዓ.ም. ሶስተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ ባሉት ሶስት በጀት ዓመታት የተከናወኑ ስራዎችን ነው፡፡

14. የክትትል ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲሆን፣ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከአራቱ የአገልግሎቱ ሪጅኖች ማለትም (ከአዲስ አበባ ሪጅን፣ ከኦሮሚያ ሪጅን፣ ከድሬደዋ ሪጅን፣ ከሀረር እና ከጅጅጋ ሪጅን) ከሚገኙ አስራ አንድ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ማለትም (ከሰሜን አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 4 እና 5 ፣

ከደቡብ አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 6፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ከደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 4፣ ከአዱላላ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል፣ ከዱከም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል፣ ከገላን የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል፣ ከደብረዘይት የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 1፣ ፣ ከሀረር የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 1፣ ከጅግጅጋ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 1 እና ከድሬደዋ ሪጅን

15. እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከአገልግሎቱ 10 የሆስፒታል ደንበኞች መካከል ከአምስቱ ማለትም (ከራስ ደስታ ሆስፒታል፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ከመሀተመ ጋንዲ ሆስፒታል፣ ከሳቢያን ሆስፒታል/ድሬደዋ ከተማ/ እና ከጀጉላ ሆስፒታል/ሐረር ከተማ/)፣ ከአገልግሎቱ 8 የባንክ ደንበኞች መካከል ከስድስቱ ማለትም (ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት፣ ከአዋሽ ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ፣ ከአባይ ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ፣ ከቡና ባንክ ሐረር ቅርንጫፍ፣ ከንብ ባንክ ሐረር ቅርንጫፍ እና ከአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ ጅጅጋ ቅርንጫፍ)፣ ከአገልግሎቱ 8 የፋብሪካ ደንበኞች መካከል ከአምስቱ ማለትም (ከድሬደዋ የምግብ ኮምፕሌክስ፣ ከድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ከኮከብ ዱቄት ፋብሪካ፣ ከምስራቅ ዱቄት ፋብሪካ እና ከቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ) እንዲሁም ከአገልግሎቱ 6 የሆቴል ደንበኞች መካከል ከሁለቱ ማለትም (ከኢትዮጵያ ሆቴልና ኢንተር ኮንትኔንታል ሆቴል) የክትትል ኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክትትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

16. የክትትል ኦዲቱን ለማከነወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

2.1 ከቆጣሪ አሰጣጥ እስከ ቢል አሰባሰብ ድረስ ያለው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤

አዲስ ኃይል ፈላጊ ደንበኞች በቅደም ተከተላቸው መሰረት እየተስተናገዱ መሆኑን በተመለከተ፣

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

17. አገልግሎቱ አዳዲስ የኃይል ፈላጊ ደንበኞችን መዝግቦ ሊይዝና በከፈሉበት ቀን ቅደም ተከተል መሰረት ማስተናገድ እንዳለበት በሪቴል ቢዝነስ የደንበኞች ፓሊሲና ፕሮሲጀር ላይ የተገለፀ ሲሆን በኦዲቱ በናሙና በታዩት 15ቱም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የኃይል ፈላጊ ደንበኞች ስም ዝርዝር ደንበኞች ሊያዩበት በሚችል ቦታ ላይ የሚለጠፍበት ሁኔታ ቢኖርም ኃይል ያገኙ ደንበኞችን በወቅቱ ከወረፋ ዝርዝር ውስጥ በማስወጣት የወረፋ መረጃውን የማሻሻል ስራ በተጠናከረ መልኩ የሚሰራበት ሁኔታ አለመኖሩን በኦዲት ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

18. አገልግሎቱ አዲስ ኃይል ፈላጊ ደንበኞች የአገልግሎት ክፍያ የፈጸሙበትን ወቅት መሰረት ባደረገ መልኩ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ወጥነት ያለው እና የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የስነ ምግባር ብልሹነት በሚያሳዩ ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድበትን ስርዓት በማመቻቸት የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽነት እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

19. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (ከዚህ በኃላ አገልግሎቱ እየተባለ የሚገለፀው) ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

20. በሰሜን አዲስ አበባ ሪጅን ደ/አ/መ/ማዕከላት የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ደንበኞችን ያለቅደም ተከተላቸው የሚስተናገዱበት ሁኔታ መኖሩን፤ እንዲሁም በአንዳንድ ማዕከላት የደንበኞች የቆጣሪ ቅደም ተከተል ሳይጠበቅ የሚያስተናግዱበት አሰራር እንዳለ፣

21. በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን ደ/አ/መ/ማዕከላት የተቋሙን መመሪያ በመተላለፍ በቁጥር 24 የሚሆኑ ደንበኞች ያለቅደም ተከተላቸው የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ የተደረገበት ሁኔታ መኖሩን፣

22. በቀድሞ ሰሜን ምስራቅ ሪጅን በኮምቦልቻ ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማግኘት ያመለከቱና የግምት ሂሳብ ከፍለው አገልግሎቱን በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ በቁጥር 1,664 የሚሆኑ ደንበኞች እያሉ ማዕከሉ ከ2007-2009 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ያመለከቱትን ደንበኞች ያለቅደም ተከተላቸው እያስተናገደ የሚገኝበት ሁኔታ መኖሩን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት የአዲስ ደንበኞች መስተንግዶ በከፈሉበት ቅደም ተከተል መሰረት እና ተቋሙ ባስቀመጠዉ የአገልግሎት ቅድም ተከትል መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ ክትትል በማድረግ ቅደም ተከተላቸውን በሚያዛቡ ላይ ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድ እንደሆነና በቀጣይ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ስለሚኖር በአብዛኛው አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ችግሩ የሚቀረፍ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

<u>**የደንበኞች መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣**</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

24. በናሙና ከተወሰዱ 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከምስራቅ ሪጅን ሀረር የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 1 እና ከገላን የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል በስተቀር በሌሎቹ 13ቱ ማዕከላት ያለው የደንበኞች መረጃ አያያዝ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በሚያመች ሁኔታ የተደራጀ ያለመሆኑ፣ እንዲሁም በኦዲቱ በናሙና በታዩት በሁሉም አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የደንበኞችን መረጃ በኮምፒውተር አደራጅቶ የመያዝ ሁኔታ ያልተጀመረ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

25. አገልግሎቱ በተቋሙ ስር የሚገኙ ሪጅኖች፣ ዲስትሪክቶች እና የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሚጠቀሙበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የሰፈነበት በማድረግ የደንበኞቹን እርካታ ሊያሳድግ እና በመረጃ ላይ የተደገፈ ፈጣንና ፍትኃዊ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

26. አገልግሎቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

27. በናሙና ከታዩት የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ውስጥ በሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 6፣ በደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9፣ በምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 6፣ በዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ በሀረር ሪጅን ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ በጅግጅጋ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 እና የድሬደዋ ሪጅን የሚገኙ የደንበኞችን ፋይል በአግባቡ በማጠናቀር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ የማይያዝ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. በደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 7፣ ቁጥር 9 እና ቁጥር 3፣ በምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና ቁጥር 6 እንዲሁም በኦሮሚያ ሪጅን በቡራዩና በዱከም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የደንበኛ ፋይልና መረጃ አያያዝ በስርዓት ያልተደራጀና በአግባቡ ያልተያዘ በመሆኑ ምክንያት ቆጣሪ ለማዘዋወር፣ የተበላሸ ቆጣሪ ለመቀየርና የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት አስቸጋሪ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

29. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በሀገሪቱ ካሉት 517 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት አብዛኛው በERP ሲስተም ስለሚሰሩ ሙሉ የደንበኞች መረጃ በሲስተም እንደሚያዝና በERP በማይገናኙ

ማዕከላት ላይ የደንበኞች መረጃ በኮምፒውተር ዳታ ቤዝ እንዲያዝ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ምስል 1. በናሙና ባየናቸው የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የደንበኛ ፋይልና መረጃ አያያዝ

<u>ደንበኞች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን በተመለከተ፣</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

30. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት 6 ሪጅኖች በሪቴል ቢዝነስ የደንበኞች ፖሊሲና ፕሮሲጀሩ በተቀመጠው የአገልግሎት መስጫ ጊዜ ሰሌዳ/ስታንዳርድ/ መሰረት ሳይሆን አገልግሎቱን ለማግኘት ከአመታት በላይ የሚፈጅ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡
31. አገልግሎቱ ለደንበኞች/ተገልጋዮች ተደራሽና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችለው በጥናት እና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ግብዓቶችን/ቁሳቁሶችን፣ ለባለሙያዎች የስራ መተግበሪያ

ግብዓቶችን በማሟላት ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ (ስታንዳርድ) መሰረት የኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅርቦቱን ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

32. አገልግሎቱ ጉዳዩን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- **በአዲስ አበባ ሪጅን**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም ለ217,084 ነጠላ ፌዝ እና ለ11,875 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ228,959 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ ለ52,691 (24.27%) ነጠላ ፌዝ እና ለ3,756 (31.63%) ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ56,447 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት በአጠቃላይ የእቅዱን 24.66% ብቻ ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም ለ59,834 ነጠላ ፌዝ እና ለ6,039 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ65,873 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ ለ57,256 (95.69%) ነጠላ ፌዝ እና ለ2,611 (43.23%) ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ59,867 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት በአጠቃላይ የእቅዱን **90.80%** ማከናወኑ፣
  - ✓ ይሁን እንጂ የሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱ በ438.66% ዝቅ ያለ መሆኑ፣
- **በደቡብ ሪጅን (ሀዋሳ)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም ለ46,980 ነጠላ ፌዝ እና ለ3,348 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ50,328 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ ለ25,099 ነጠላ ፌዝ እና ለ625 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ25,724 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት በአጠቃላይ የእቅዱን 51.1% ብቻ ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም ለ34,971 ነጠላ ፌዝ እና ለ1,699 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ36,670 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ ለ11,174 ነጠላ ፌዝ እና ለ359 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ ለ11,533 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት በአጠቃላይ የእቅዱን 31.45% ብቻ ማከናወኑ፣

- ✓ የሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱ በ137.24% ዝቅ ያለ መሆኑ፣

- **በሰሜን ሪጅን (መቀሌ)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 46,980 ነጠላ ፌዝና 3,348 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 50,328 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 28,693 ነጠላ ፌዝና 303 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 28,996 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት በአጠቃላይ የእቅዱን **57.6%** ማከናወኑ፣
  - ✓ በ 2010 ዓ.ም 38,565 ነጠላ ፌዝና 1,699 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 40,264 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 16,223 ነጠላ ፌዝና 191 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 16,414 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **40.77% ብቻ** ማከናወኑ፣
  - ✓ የሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **124.99%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣
- **በምዕራብ ሪጅን (ጅማ)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 30,876 ነጠላ ፌዝና 2,856 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 33,732 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 14,958 ነጠላ ፌዝና 515 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 15,473 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **45.9%** ማከናወኑ፣
  - ✓ በ 2010 ዓ.ም 24,830 ነጠላ ፌዝና 1,453 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 26,283 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 8,923 ነጠላ ፌዝና 166 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 9,089 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **34.58%** ማከናወኑ፣
  - ✓ ሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **128.34%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣
- **በሰሜን ምዕራብ ሪጅን (ባህር ዳር)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 58,932 ነጠላ ፌዝና 3,984 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 62,916 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 21,883 ነጠላ ፌዝና 728 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 22,611 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **35.9%** ማከናወኑ፣

- ✓ በ2010 ዓ.ም 31,755 ነጠላ ፌዝ፣ 2,017 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 33,772 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 15,765 ነጠላ ፌዝና 746 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 16,511 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **48.89%** ማከናወኑ፣
- ✓ ሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **186.29%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣

- **በደቡብ ምስራቅ ሪጅን (አዳማ)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 76,920 ነጠላ ፌዝና 5,783 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 82,703 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 20,855 ነጠላ ፌዝና 294 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 21,149 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **25.6%** ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 30,727 ነጠላ ፌዝና 2,917 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 33,644 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 16,401 ነጠላ ፌዝና 353 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 16,754 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **49.8%** ብቻ ማከናወኑ፣
  - ✓ ሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ 2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **245.8%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣
- **በጅጅጋ ሪጅን**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 5,460 ነጠላ ፌዝ፣ 300 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 5,760 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 3,196 ነጠላ ፌዝና 65 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 3,261 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **56.6%** ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 3,420 ነጠላ ፌዝና 175 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 3,595 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 2,659 ነጠላ ፌዝና 36 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 2,695 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **74.97%** ማከናወኑ፣
  - ✓ ሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ 2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **160.2%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣

- **በምስራቅ ሪጅን (ድሬዳዋ)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 30,300 ነጠላ ፌዝና 2,035 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 32,335 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 12,201 ነጠላ ፌዝና 351 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 12,552 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን 38.8% ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 22,073 ነጠላ ፌዝና 1,043 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 23,116 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 9,002 ነጠላ ፌዝና 186 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 9,188 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን 39.75% ብቻ ማከናወኑ፣
  - ✓ ሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ 139.88% ዝቅ በማድረግ አቅዶ የፈጸመ መሆኑ፣
- **በሰሜን ምስራቅ ሪጅን (ደሴ)**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 34,462 ነጠላ ፌዝና 2,078 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 36,540 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ 18,210 ነጠላ ፌዝና 326 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 18,536 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን 50.7% ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 28,082 ነጠላ ፌዝና 1,064 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 29,146 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 11,729 ነጠላ ፌዝና 169 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 11,898 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን 40.82% ብቻ ማከናወኑ፣
  - ✓ ሪጅኑ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ 125.36% ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣
- **በአሶሳ ሪጅን**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 8,500 ነጠላ ፌዝና 1,500 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 10,000 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 4,055 ነጠላ ፌዝና 98 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 4,153 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን 41.5% ብቻ ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 4,279 ነጠላ ፌዝና 775 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 5,054 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 3,480 ነጠላ ፌዝና 80 ባለ ሶስት

ፌዝ በድምሩ 3,560 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **70.44%** ማከናወኑ፣

- ✓ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **197.86%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ፣

- **በሰመራ ሪጅን**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 3,516 ነጠላ ፌዝና 492 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 4,008 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 1,705 ነጠላ ፌዝና 54 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 1,759 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **43.9%** ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 1,929 ነጠላ ፌዝና 271 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 2,200 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 1,863 ነጠላ ፌዝና 111 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 1,974 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **89.73%** ማከናወኑ፣
  - ✓ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **182.18%** ዝቅ በማድረግ ያቀደ መሆኑ
- **በጋምቤላ ሪጅን**
  - ✓ በ2009 ዓ.ም 6,780 ነጠላ ፌዝና 1,344 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 8,124 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 4,657 ነጠላ ፌዝና 124 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 4,781 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **58.9%** ማከናወኑ፣
  - ✓ በ2010 ዓ.ም 4,881 ነጠላ ፌዝና 697 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 5,578 ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 4,665 ነጠላ ፌዝና 181 ባለ ሶስት ፌዝ በድምሩ 4,816 ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት የእቅዱን **86.88%** ያከናወነ መሆኑ፣
  - ✓ የ2010 ዓ.ም ዕቅድ ከ2009 ዓ.ም ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር እቅዱን በ **145.64%** ዝቅ በማድረግ ማቀዱ፣

ከ2009 እና 2010 ዓ.ም የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የዝቅተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት ለመካከለኛ በ45 ቀናት እና ለከፍተኛ በ60

ቀናት ውስጥ ቆጣሪ የማስገባት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና ቁጥር 6፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 6፣ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል እና ከቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1 ከድሬደዋ ሪጅን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. አገልግሎቱ በስሩ በሚገኙ ሪጅኖች የቆጣሪና የትራንስፎርመር ለማስገባት ተመዝግበው አስፈላጊውን ክፍያ ከፍለው የሚጠባበቁ የዝቅተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች ፍላጎትን በተመለከተ ምን ያህል ደንበኞች ከመቼ ጀምሮ ተመዝግበው እየተጠባበቁ እንዳሉ እንዲሁም ምን ያህሉ ደንበኞች አገልግሎት እንዳገኙ ለመገምገም በዋናው መ/ቤት መረጃዎችን ማግኘት ያልተቻለ ቢሆንም በናሙና ከታዩ ሪጅኖች እና ደ/አ/መ/ ማዕከላት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለው፡-

- በኦሮሚያ ሪጅን በገላን ከ2008 ጀምሮ፣ በአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ፣ በቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ፣ በዱክም፣ በአሰላ፣ በዶዶላ እና በቡራዩ ደ/አ/መ/ማዕከላት ከህዳር 25/2010 ዓ.ም ጀምሮ፣ በሶከሩ ማዕከል፣ ሻሸመኔ ቁጥር 2 ፣ በሱልልታ ማዕከል፣ በቀርሳ ማዕከል፣ በጅማ ማዕከልና በጉለስ ማዕከል ስር የሚገኙ በቁጥር 4,186 የአገልግሎቱ ደንበኞች የነጠላ ፌዝ እና የባለ ሶስት ፌዝ ቆጣሪ ለማስገባት ሙሉ ክፍያ የከፈሉ ቢሆንም አገልግሎት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ግዜ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ሪጅን በደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-3 ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ፣ ቁጥር-9 ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ፣ ቁጥር 3፣ ቁጥር 4፣ ቁጥር 6 እና ቁጥር 7 ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ እና ቁጥር 1 ከ2008 ጀምሮ፣ በሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4 ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ፣ ቁጥር-6 ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ፣ በሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ 3 እና 5 ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ፣ በምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1 ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ፣ ቁጥር 5 ከ2008 ዓ.ም

ጀምሮ እንዲሁም በሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከልቁጥር 5 እና በምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 ስር የሚገኙ 2,523 የአገልግሎቱ ደንበኞች የነጠላ ፌዝና የባለ ሶስት ፌዝ ቆጣሪ ለማስገባት ሙሉ ክፍያ የከፈሉ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ግዜ አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፣

- በትግራይ ሪጅን የአዲግራት ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ እና በወግዲ ደ/አ/መ/ማዕከል የሚገኙ 1,072 የአገልግሎቱ ደንበኞች የነጠላ ፌዝና የባለ ሶስት ፌዝ ቆጣሪ ለማስገባት ሙሉ ክፍያ የከፈሉ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ግዜ አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፣
- በአማራ ሪጅን የአብድራፊ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በጎንደር ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 2፣ በእብናት ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በእስቴ ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ፣ በደብረታቦር ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ፣ በደጀን ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ፣ በብቸና ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ በዳባት ደ/አ/መ/ማዕከል ከነሀሴ 2008 ዓ.ም ጀምሮ፣
- በደባርቅ ማዕከል፣ በጋሻና ማዕከል ፣ በቻግኒ ማዕከል፣ ላሊበለ ማዕከል፣ በሰቆጣ ማዕከል፣ በከለላ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በአቅስታ ማዕከል፣ በመካነ ሰላም ማዕከል፣ በላንታ ማዕከል፣ በወገልጤና ማዕከል እና በሀይቅ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚገኙ 16008 የአገልግሎቱ ደንበኞች የነጠላ ፌዝና የባለ ሶስት ፌዝ ቆጣሪ ለማስገባት ሙሉ ክፍያ የከፈሉ ቢሆንም አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፤
- በጅግጅጋ ሪጅን በቀብሪበያ ደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚገኙ 200 የነጠላ ፌዝ ደንበኞች ሙሉ ክፍያ የከፈሉ የሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፤ በቤንሻንጉል ሪጅን በባምቢስና በቀኖሌካብ ደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚገኙ 244 የነጠላ ፌዝና 4 ባለ ሶስት ፌዝ ደንበኞች ክፍያ ከፍለው አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፤
- በምስራቅ ሪጅን በድሬደዋ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1 የሚገኙ 177 የነጠላ ፌዝ ሙሉ ክፍያ የከፈሉ የሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች የሚገኙ ቢሆንም 79 ደንበኛ ብቻ አገልግሎት ማግኘት የቻለ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የተቋሙ የዲስትሪቢውሽን ዕቃ አቅርቦት በዋናነት ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በነበረው ውል የሚቀርብ በመሆኑ በሚቀርበው ዕቃና በዕቅድ ፍላጎት መካከል ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር ያጋጥም ስለነበረ በዕቅድና በአፈጻጸም ልዩነት ሊፈጠር እንደቻለ፡፡ በ2010 በጀት ዓመት የተያዘውን ዕቅድ ሊኖር የሚችለውን የዲስትሪቢውሽን ዕቃዎች አቅርቦት ታሳቢ በማድረግ በመሆኑ ዕቅዱ ከ2009 ዕቅድ ጋር ዝቅ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

36. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ በየግዜው አገልግሎቱ በየማዕከላቱ በርካታ አዳዲስ ደንበኞችን በመቀበል ለመመዝገቢያ እና አዲስ ቆጣሪና ትራንስፎርመር እንዲሁም ተያያዥ የዕቃዎች ግምት በማውጣት ክፍያ ተቀብሎ ለበርካታ አመታት አገልሎት ሳይሰጥ የሚቀመጥና በደንበኞች ላይም ቅሬታና እንግልት እየፈጠረ በመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>ለደንበኞች የሚሰጠው የትራንስፎርመር ተከላ እና ማሻሻያ አገልግሎት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ /በስታንደርዱ/ መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

37. አገልግሎቱ ባዘጋጀው አዲስ የኃይል አቅርቦትና የኃይል ማሻሻያ ፕሮሲጀር ላይ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያስችለው ዘንድ በጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ለመስጠት ካቀዳቸው ስራዎች መካከል የትራንስፎርመር ተከላ እና ማሻሻያ አገልግሎት ለሚጠይቁ ደንበኞች በ3 ወር ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱን ለመስጠት ቢሆንም፣ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት 6 ሪጅኖች የትራንስፎርመር ተከላ እና የትራንስፎርመር ማሻሻያ አገልግሎት ለመስጠት ከአንድ አመት በላይ እንደሚወስድባቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

38. አገልግሎቱ ለደንበኞች/ተገልጋዮች ተደራሽና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችለው በጥናት እና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ግብዓቶችን/ ቁሳቁሶችን፣ ለባለሙያዎች የስራ መተግበሪያ ግብዓቶችን በማሟላት ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ (ስታንዳርድ) መሰረት የኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅርቦቱን ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

39. አገልግሎቱ ጉዳዩን በተመለከተ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

40. አገልግሎቱ በ 2009 ዓ.ም 2,031 የአዲስ ትራንስፎርመሮች ተከላ በማከናወን የእቅዱን 48% አፈፃፀም ማሳየቱን፣ በተጨማሪም 521 ትራንስፎርመሮችን የማሻሻል ስራ በመስራት የእቅዱን 36.6% ማከናወኑን፣

41. አገልግሎቱ ትራንስፎርመር ተከላ ለሚጠይቁ ደንበኞች የትራንስፎርመር እና የማቴሪያል እጥረት በመኖሩ በ3 ወር ግዜ ውስጥ የትራንስፎርመር ተከላ አገልግሎት እንዲያገኙ የማይደረግ መሆኑን በናሙና ከታዩ የምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ ማዕከል ቁጥር-4፣ የሰሜን አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና 6፣ የደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ የምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ የዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ የሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የጅግጅጋ የደ/አ/መ/ማዕከል እና የድሬዳዋ ሪጅን ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲሁም የራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታልና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬዳዋ ዲስትሪክት ለሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

42. የድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ፍብሪካ የትራንስፎርመር ብልሽት (ዘይት ማፍሰስ) አስከትሎ ማሻሻያ ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

43. በኦሮሚያ ሪጅን በዱከም የደ/አ/መ/ ማዕከል 21 የተለያዩ ደንበኞች ከ 2004 ዓ.ም ጀምሮ፣ በሱማሌ ሪጅን 21 ደንበኞች ከየካቲት 2009 ጀምሮ፣ በድሬደዋ ሪጅን 26 ደንበኞች ከሚያዚያ 2009 ጀምሮ፣ በሀረር ሪጅን 8 ደንበኞች፣ በሰሜን አዲስ አበባ 3 ደንበኞች ከታህሳስ 2004 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ ትራንስፎርመር ለማስገጠም ክፍያ የከፈሉ የሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች ቢኖሩም አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፣

44. በደቡብ ሪጅን በሚዛን ደ/አ/መ/ማዕከል የሚገኙ ደንበኞች ለአዲስና ለማሻሻያ 14 ትራንስፎርመር እና ለጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር የ6 ትራንስፎርመር ማሻሻያ

ለማድረግ አስፈላጊውን ክፍያ የከፈሉ የሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች ቢኖሩም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ግዜ አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፤

45. በምዕራብ ሪጅን በጌራ ደ/አ/መ/ማዕከል ለኦሞ ፈንታሌ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ፕሮጀክት DC- 20/04 የግመት ሂሳብ ብር 364897.52 የቀበሌ ነዋሪዎቹ በጋራ በማዋጣት በግንቦት 2004 ዓ.ም በደረሰኝ ቁጥር 89591 ክፍያ የፈጸሙ ቢሆንም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የተቋሙ የዲስትሪቢውሽን ዕቃ አቅርቦት በዋናነት ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በነበረው ውል የሚቀርብ በመሆኑ በሚቀርበው ዕቃና በዕቅድ ፍላጎት መካከል ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር ያጋጥም የነበረ ሲሆን በ2011 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ ተቋሙ የሀገር ውስጥ አምራቾችን በግልጽ ጨረታ በመጋበዝ እና በማወዳደር ውል ወስዶ አቅርቦቱን ሊያሻሽል የሚችል ሰፊ ስራ እንደተሰራ እና ከፍለው የሚጠባበቁ ደንበኞችን በተያዘው በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለማስተናገድ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

47. አገልሎቱ ይህን ይበል እንጂ ስለመሰራቱ ለኦዲት ቡድኑ የቀረበ ምንም አይነት ማስረጃ የለም፡፡

<u>በቆጣሪ ንባብ ባለሙያነት ለተሰማሩ የድርጅቱ ሠራተኞች የስራ መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ፣</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

48. የቆጣሪ ንባብ ስራ ላይ ተሰማሩ ባለሙያዎች የሚሰሩትን ስራ ተጠያቂነት በሰፈነበት መልኩ በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የሚያስቸላቸው የስራ መመሪያ በድርጅቱ በኩል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ የተደረገበት ሁኔታ ቢኖርም በኦዲቱ ወቅት በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የንባብ ባለሙያዎችን በተጠናከረ መልኩ ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

49. አገልግሎቱ የቆጣሪ አንባቢያን ያላቸውን የስራ ሁኔታን ያገናዘበ ስራቸውን በአግባቡ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል፣ የተጠናከረና ውጤታማ የሆነ

ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርገበት እንዲሁም የቆጣሪ አንባቢያኑ ለሚፈጽሙት የስራ ላይ ጥፋቶች ተገቢ እና ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችል፣ የሚሰራው ስራ ጥራት የጠበቀ እንዲሆን አንድ የቆጣሪ አንባቢ ምን ያህል ቆጣሪ ሊያነብ እንደሚገባ በግልጽ የሚያሳይ እና በወቅቱ ካለው የተቋሙ አደረጃጀት ጋር በተጣጣመ መልኩ ክለሳ ሊደረግበት የሚችል የቆጣሪ አንባቢያን የስራ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

50. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

51. በሰሜን ምስራቅ በሀይቅ ደ/አ/መ/ማዕከል የሚገኙ ሁለት የቆጣሪ አንባቢዎች የደንበኛውን ቆጣሪ ሳያነቡ በግምት በቆጣሪ ንባብ ደብተር ላይ በመመዝገብ የተጋነነና የኔጌቲቭ ቢሎች ቁጥር እዲጨምር ማድረጋቸው፤ የኢንስፔክሽን ስራ ባለመሰራቱና ቆጣሪ አንባቢዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው የኤሌክትሪክ ስርቆት እየተበራከተ መምጣቱ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. በዱከም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ለ13,000 ደንበኞች 10 አንባቢዎች የሚገኙ ቢሆንም የቆጣሪ አንባቢዎችን የሚቆጣጠር ሱፐርቫይዘር አለመኖሩን፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ቁጥር-4 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የቆጣሪ አንባቢዎችን የሚከታል ሱፐርቫይዘር የሌለ መሆኑ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የቆጣሪ ንባብን ለማሳለጥ እንዲቻል አንድ ቆጣሪ አንባቢ ምን ያህል ቆጣሪዎችን ማንበብ እንደሚችል በተቋም ደረጃ ጥናት በማድረግ አንድ ቆጣሪ አንባቢ በወር 2200 ደንበኞችን እንዲያነብ መደረጉን ፣ ከ5000 በላይ ደንበኞች ለሚገኙባቸዉ አካባቢዎችና ከተሞች አንድ እና ከዚያ በላይ የቆጣሪ አንባቢ ሱፐር ቫይዘር እንዲኖር መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን፣ ለቆጣሪ አንባቢዎች በክልል እና በኮርፖሬት

ደረጃ በመጡ የተቋሙ አመራረሮች ሰፊ የቅስቀሳ እና የስልጠና ስራዎች መሰራታቸውን፣

54. እንዲሁም የቆጣሪ ንባብ ኃላፊነትን በአግባቡ በማይወጡ አንባቢዎች ላይ በተቋሙ ደንብ መሰረት ከቃል ማስጠንቀቂያ አንስቶ እንደጥፋቱ ድግግሞሽ እና አይነት እርምጃ እንደተወሰደ፣ በየአካባቢዎቹ የነበረውን የአንባቢ እጥርት ለመፍታት በበጀት አመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ሰዉ ኃይሉ በዉስጥ እድገት ዝዉዉር እና ቅጥር እንዲሟላ ለማድረግ በተደረገዉ ጥርት በሪፖርቱ በቀረቡት አካባቢዎች እና በሌሎችም በክልሉ በሚገኙ አካባቢዎች ሙሉ ለሙሉ የቆጣሪ አንባቢ ችግር እንዲፈታ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

55. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ ስራው ስለመሰራቱ በክትትል ኦዲቱ ወቅት መመልከት ያልተቻለ ሲሆን አንድ ቆጣሪ አንባቢ በወር 2200 ደንበኞችን እንዲያነብ ፣ ከ5000 በላይ ደንበኞች ለሚገኙባቸዉ አካባቢዎችና ከተሞች አንድ እና ከዚያ በላይ የቆጣሪ አንባቢ ሱፐር ቫይዘር እንዲኖር የተዘጋጀው መመሪያ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ለኦዲት ቡድኑ ተልኳል፡፡

<u>አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኙ ደንበኞች ወደ ክፍያ ስርዓት እንዲገቡ ማድረግን በተመለከተ፣</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

56. በኦዲት በናሙና በታዩት 6 ሪጅኖች አዲስ ኃይል ያገኙ ደንበኞች በደንበኞች ፓሊሲና ፕሮሲጀር በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ወደ ክፍያ ስርዓት እንዲገቡ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

57. አገልግሎቱ ዲስትሪክቶች እና ሪጅኖች ላይ ተጠያቂነት ሊያሰፍን የሚችል ለክትትል እና ቁጥጥር ስራ አመቺነት የሚፈጥር በሚመለከታቸው የውስጥ እና ውጭ ባለድርሻ አካላት ውይይት ተደርጎበት እና በማሻሻያ ሃሳቦች ዳብሮ ተግባራዊ የሚደረግ አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ያገኙ ደንበኞችን በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ወደ ክፍያ ስርዓት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው የሚያሳይ ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና ለተግባራዊነቱም ተከታታይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

58. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

59. የአዲስ ደንበኛ ፋይል በወቅቱና በአግባቡ ተዘጋጅቶ በመላክ ወደ ሲስተም የማይገባ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ሀይል እየተጠቀሙ ቢል የማይወጣላቸው በርካታ ደንበኞች መኖራቸው፣ አንዳንድ ከፍተኛ የሀይል ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎችም በወቅቱ ቢል የማይወጣላቸው በመሆኑ የተጠቀሙበትን ኢነርጂ ክፍያ መፈፀም አለመቻላቸውን፣

60. በሰሜን ምዕራብ ሪጅን 858 ፣ በሰሜን ምስራቅ ሪጅን በጊሸራቤል ደ/አ/መ/ማዕከል 17፣ በምስራቅ ሪጅን በባቢሌ ደ/አ/መ/ማዕከል 42 እና በጉርሱም ደ/አ/መ/ማዕከል 195 ፣ በደቡብ ሪጅን በርባ ደ/አ/መ/ማዕከል 2፣ በአሶሳ ሪጅን በአምጦ ደ/አ/መ/ማዕከል 14፣ በቤንሻንጉል ሪጅን በባምቢስ ደ/አ/መ/ማዕከል ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ 33፣ በኦሮሚያ ሪጅን የጫንጮ ደ/አ/መ/ማዕከል 100 እና የአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል 30፣ በአማራ ሪጅን በደንበጫ ደ/አ/መ/ማዕከል 14 ፣ በጋሻና ደ/አ/መ/ማዕከል 17፣ በአማኑኤል ደ/አ/መ/ማዕከል 19 እና በደሴ ዲስትክት 1087 አዳዲስና ነባር ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት እያገኙ መረጃቸው ወደ ሲስተም ባለመግባቱ ለበርካታ ወራት ቢል የማይወጣላቸው መሆኑ፣

61. በምዕራብ ሪጅን በጮራ ደ/አ/ማዕከል በውል ቁጥር 12252 የተመዘገበው የጮራ ውሃ ልማት ከታህሳስ 4/2007 እስከ ጥቅምት 2/2009 ድረስ የተጠቀመበትን የፍጆታ ሂሳብ ብር 20405.87 ሲስተም ላይ በማቋረጥ ቢል እንዳይወጣ የተደረገ መሆኑ፣

62. በምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን የሚገኘው የውል ቁጥር 701620 የቆጣሪ አይነት 300/5፣ የውል ቁጥር 704121 የቆጣሪ አይነት 200/5፣ የውል ቁጥር 704804 የቆጣሪ አይነት 1000/5 እና የውል ቁጥር 704490 የቆጣሪ አይነት 1000/5 እንደ ቅደም ተከተላቸው በግንቦት 4/2007፣ መጋቢት 2/2007፣ መስከረም 26/2008 እና መጋቢት 11/2008 ቆጣሪው ተተክሎ እየሰራ ቢሆንም ቢል የማይዘጋጅ መሆኑ፣

63. በዱክም ዲስትሪክት አገልግሎት መስጫ ማዕከል ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ካገኙ በኋላ ቢል በአማካኝ ለማዘጋጀት አምስት ወራት የሚወስድ መሆኑን ማዕከሉ

በቀን 26/3/2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 67.2/44/10 ለዋናው መ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ማሳወቁን፣ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በቀጣይ የERP ሲስተም ወደ ስራ የሚገባ በመሆኑ በቀድሞ ሲስተም የሚታዩ ችግሮችን ከማስቀረት በተጨማሪ ለሚሰሩ አዲስ ሀይል ማገናኘት ስራዎች በወቅቱ ቢል መውጣቱን ለመከታተልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚያስችል እንዲሁም አገልግሎት አግኝተው መረጃቸው ወደ ሲስተም እንዲገባ ባለመደረጉ ክፍያ የማይፈጽሙ ደንበኞች አንዳሉ በቀረበው መሰረት ለችግሩ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በመስራት በበጀት ዓመቱ ስምንት በክልሉ መሰል ችግሮችን በስፋት በመለየት እና መፍትሄ ለመስጠት በተደረገው ጥረት በድምሩ 14867 ደንበኞችን መረጃቸውን ወደ ሲስተም እንዲገባና ቢል እንዲወጣላቸው እንደተደረገ ገልጸዋል፡፡

65. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ የተሰራ ስራ ስለመኖሩ ለኦዲት ቡድኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>አገልግሎቱ ለሰጠው አገልግሎት በወቅቱ ክፍያ መሰብሰቡን በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

66. አገልግሎቱ ከተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ግለሰብ ደንበኞቹ ከ10 ዓመታት በፊት ጀምሮ ክፍያ ሳይፈጸምባቸው በየበጀት ዓመታቱ ተንከባሎ የመጣ ብር 132,352,369.89 በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ያልሰበሰበ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከደንበኞቹ ሊሰበስበው የሚገባ በሚሊዮን የሚቆጠር የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ አለመሰብሰቡ ተገኝቶ ነበር፡፡

67. በሃገሪቷ እየተስፋፉ ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ለህብረተሰቡ በበቂ ሁኔታ ለማዳረስ ብሎም ለጎረቤት ሀገሮች የሃይል አቅረቦቱን ለማሰራጨት መንግስት ከፍተኛ የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎችን እየገነባ ያለበት ሁኔታ ሲኖር ለዚህ ስራ የሚሆን የፋይናንስ ምንጭ በበቂ ሁኔታ እንዲኖር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ቀልጣፋና፤ ውጤታማ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰቢያ ስርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

68. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

69. በ2009 በጀት ዓመት የኤሌክትሪክ አገልግሎት በቋሚነትና በግዜያዊነት ከተቋረጠባቸው ደንበኞች ያልተሰበሰበ ውዝፍ የፍጆታ ሂሳብ ብር 84,240,008.25 የሚገኝ ሲሆን ከእነዚህም መካከል በጥቂቱ ለማሳየት ያህል፡-

- ✓ በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን ብር 5,147,664.40 ፣ በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ብር 5,669,589.08፣ በደቡብ ሪጅን ብር 6,276,951.30፣ በጅግጅጋ ሪጅን ብር 4,146,206.85፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን ብር 1,986,802.53፣ በምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4 ብር 85,441.67፣ በአማራ ሪጅን የባህር ዳር ደ/አ/መ/ማዕከል ቁትር 1 ብር 1,807,845.28፣ የዳባት ደ/አ/መ/ማዕከል ብር 319,051.88፣ የደባርቅ ደ/አ/መ/ማዕከል ብር 24,081.74፣ በአዲስ አበባ ሪጅኖችና በደቡብ ምስራቅ ሪጅኖች ከመንግስት ቢሎች ብር 66,752,020.41 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

70. በ2010 ዓ.ም በአገልግሎቱ በውስጥ ኦዲት ሪፖርት መሰረት ከተቋሙ የቢሊንግ ሲስተም መረጃ መሰረት ለአንድ ዓመትና ከአንድ ዓመት በላይ ያልተሰበሰበ የቢል ሂሳብ ብር 579,273,386.54 መገኘቱ፣ ከእነዚህም ያልተሰበሰበ የቢል ሂሳብ መካከል በጥቂቱ ለማሳየት ያህል፡-

- ✓ ከግለሰቦች፣ ከመንግስትና ከኢንዱስቱሪ ደንበኞች በምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ብር 28,259.07 ፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን ብር 22,995,620.46 ፣ በአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 11 ክልል ከአማኑኤል የትልቅ ውሃ ጉድጓድ ብር 4,695,834.66 ፣ በአዲስ አበባ ሪጅኖችና በደቡብ ምስራቅ ሪጅኖች ብር 66,752,020.41፣ በሰሜን ምዕራብ ሪጅን የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4 ብር 55,948 እና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ቁጥር 4 ብር 55,948 ዋጋ ያላቸው ያልተሰበሰቡ ቢሎች የተገኙ መሆኑ፣

- ✓ በቢሾፍቱ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር-1 ስር የሚገኘው ጋፋት አርማመንት ኢኒዱስትሪ በተለያየ ውል ተዋውለው በገባው ቆጣሪ የጥቅምት 2011 ዓ.ም ለተጠቀሙበት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ ብር 1,942,491.38/ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ሁለት ሺ አራት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከ 38/100 ሳንቲም/ ውዝፍ ሂሳብ አለመክፈላቸውን፣
- ✓ እንዲሁም በቢሾፍቱ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር-1 ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ አየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ በተለያየ ውል ተዋውለው በገባው ቆጣሪ የህዳር 2011 ዓ.ም ለተጠቀሙበት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ሂሳብ ብር 3,003,610.42/ ሶስት ሚሊዮን ሶስት ሺ ስድስት መቶ አስር ብር ከ 42/100 ሳንቲም/ ውዝፍ ሂሳብ አለመክፈላቸውን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከታዩ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. በሰሜን አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር -5 ኮልፌ አጠና ተራ ተብሎ በሚጠራው አከባቢ ኮልፌ የገበያ አዳራሽ ከ 5 ዓመት በፊት ሲቃጠል በገበያ ማዕከሉ ተገጥመው የነበሩ ቆጣሪዎች የተቃጠሉ ቢሆንም ክፍያ ያልተፈፀመ እና እስካሁን ድረስ ቢል እየወጣ እንደሚገኝ፣ እንዲሁም ውዝፍ እዳው ምን ያህል እንደሆነ እንደማይታወቅ የማዕከሉ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረባላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

72. ለመንግስት ተቋማት ግንባታ ስራዎች ማለትም ለስኳር ፋብሪካዎች፣ ለባቡር፣ ለኢትዮ ተሌኮም ለቆጣሪ ማስቀጠያ ሂሳቦች ሳይከፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገቢውን ክትትል ባለመደረጉ በቢሊዮን ብር የሚገመት የማስቀጠያ ሂሳብን ጨምሮ የተጠቀሙበት የፍጆታ ሂሳብ በወቅቱ በሲስተም ተመዘዝግቦ ስለማይሰበሰብ የኃይል ብክነት ምጣኔ ከፍ እንዲል እንዳደረገውና ለተቋሙ የገንዘብ እጥረት ምክንያት እንደሆነ፤

73. በተለያዩ ዲስትሪክቶችና አካባቢዎች የሚገኙ የመንግድ መብራት ቆጣሪዎች በአግባቡ ስለማይነበቡና ቢል ስለማይወጣላቸው የፍጆታ ሂሳባቸው እየተሰበሰበ እንዳልሆነ፤

74. አገልግሎቱ ለደንበኞች በሚሰጠው አገልግሎት መሰረት በወቅቱ የቆጣሪ ንባብ በማንበብና ቢል በማውጣት ክፍያ እንደማይሰበስብ፣ ወረዳዎች የሚያደራጃቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች /ማህበራት/ ክፍያ ሳይፈፅሙ አከባቢውን ለቀው እንደሚሄዱ፣

እንዲሁም በመንገድ ስራ ምክንያት የሚነሱ ቤቶችም የተጠቀሙበትን የአገልግሎት ክፍያ ሳይፈፅሙ እንደሚሄዱ እንዲሁም በወቅቱ ከመንግስትና ከኢንዱስትሪዎች የቢል ሂሳብ የማይሰበሰብ መሆኑ ከምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4 እና የቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

75. በኦሮሚያ ሪጅን ከገላን የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ያሉ ደንበኞች ክፍያ የሚፈፅሙት አቃቂ በመሄድ እንደሆነ፣ ይሄ ለደንበኞች አመቺ ባለመሆኑ አገልግሎት ክፍያ በማይከፍሉት ላይ እርምጃ ለመውሰድ እንዳልቻሉ የማዕከሉ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በተያዘው በጀት ዓመት ውዝፍ ሂሳቦችን ለመሰብሰብ በተደረገው ከፍተኛ ጥረት 935,636,044 ብር እንደተሰበሰበ ፣ የአገልግሎት ክፍያ አሰባሰብን ከባንክ ጋር በማስተሳሰር ደንበኞች እንዲከፍሉ ለማድረግ ከንግድ ባንክ ጋር ስምምነት እንደተፈራረመ፣ የኦሮሚያ ክልል ኤሌክትሪክ ውዝፍ ገንዘብ ስብሰባ አስመልክቶ በዚህ በጀት ዓመት በ 2011 ዓ.ም ብር 186,514,758.39 በስድስ ወር እቅድ አፈፃጸም ላይ የሰበሰብብ መሰብሰቡን፣

77. የተሰበሰበውም ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ፣ ከደርባ ሲሚንቶ ፣ ከሐበሻ ሲሚንቶ ፣ ከኢስተርን ኢንደስትሪ ዞንና ሶማሌ ሪጅን፣ በተጨማሪ ከሌሎች የተቀናጀ የኢስፔክሽን ስራዎችን በማካሄድ ቢላቸው ከሲስተም ላይ ተቋርጦ ነገር ግን መብራት እያገኙ ያሉ ደንበኞችን የማጥራት ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ፣ የኢነርጂ ሽያጭ ገቢ ስብሰባን ለማሻሻል በአማራ ክልል ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አንደሆነና በበጀት አመቱ ብር 3,423,825.2 ገቢ ማድረግ የተቻለ አንደሆነና ክፍያቸዉን ለመፈጸም ፈቃደኛ ያለሆኑ ደንበኞችን በህግ አግባብት ተጠያቂ ለማድረግና ገንዘቡን ለመሰብሰብ የሚያስችል ስራ በህግ አገልግሎት በኩል እየተሰራ እንደሚገኝ፣

78. በባህር ዳር ዲስትሪክት ደንበኛ የሆኑ ሲኖ ሃይድሮ መንገድ ሥራ ተቋራጭ ብር 5,927,543.28 ባለመክፈላቸው በመዝገብ ቁጥር 50691 እና ዝጎራ ቀጭን መንገድ ፕሮጀክት ብር 1,457,205.00 ባለመክፈሉ በመዝገብ ቁጥር 50712 አብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲሁም በድሮው ሰ/ምዕ/ሪጅን በአሁኑ ጎንደር ዲስትሪክት ደንበኛ የሆኑ

ፍኖተ- የሕብረት ሥራ ማሕበር ብር 135,708.00 ብር በለመክፈሉ በመዝገብ ቁጥር 36905 ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ በክርክር ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

79. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ ከላይ ለመግለፅ እንደተቻለው በሌሎች የአገልግሎቱ ዲስትሪክቶች ያልተሰበሰበ ከፍተኛ ውዝፍ መኖሩን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት የቻለ ሲሆን አገልግሎቱ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ፣ ከደርባ ሲሚንቶ ፣ ከሐበሻ ሲሚንቶ ፣ከኦሮሚያ እና ከኢስተርን ኢንደስትሪ ዞንና ሶማሌ ሪጅን የተሰበሰቡ ገንዘቦችን በናሙና መልክ ለኦዲት ቡድኑ ልኳል፡፡

የታሪፍ ለውጥ ሊደረግባቸው የሚገቡ ደንበኞችን በወቅቱ በመለየት የታሪፍ ለውጥ መደረጉን በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

80. በኦዲቱ በናሙና ከተለዩት 6 ሪጅኖች ከ2006-2008 በጀት ዓመታት የታሪፍ ለውጥ የተካሄደባቸውን ደንበኞች ዝርዝር መረጃ ተጠይቀው ከደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን በስተቀር ሌሎች ሪጅኖች መረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፣
81. የ2008 የአገልግሎቱ የህግ ማስከበር/ኢንፎርስመንት/ የስራ ሂደት ስራ አፈጻጸም ሪፖርት በተከለሰበት ወቅት በበጀት ዓመቱ 17,101 የታሪፍ ለውጥ ለማከናወን ታቅዶ 2,303 ብቻ የተከናወነ ሲሆን፣ ይህም የእቅዱን 13 ከመቶ ብቻ መሆኑን፣
82. በሰኔ 30 2008 ዓ.ም. በአገልግሎቱ የውስጥ ኦዲት ሪፓርት መሰረት በሰሜን አዲስ አበባ ሪጅን 22 ተቋማት ትክክለኛው ታሪፋቸው 20 መሆን ሲገባው ሲስተም ላይ የተመዘገበው በስህተት 41 ተብሎ መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት ተቋሙ ብር 1,094,580.4 እንዳይሰበስብ ያደረገው መሆኑንና ይህ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ወጪ ከሆነ በኋላም በክዋኔ ኦዲቱ በተደረገው ማጣራት በ17 ተቋማት ላይ እስከ 04/04/2009 ዓ.ም. ድረስ ሲስተም ላይ የታሪፍ ለውጥ ያልተደረገ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡
83. አገልግሎቱ የሚያከናውነውን ስራ ተደራሽ እና ውጤታማ ሊያደረገው የሚያስችለው አደረጃጀት በመፍጠር፤ የቆጣሪ ማንበብ ስራ የሚያከናውኑ ስራ ፈጻሚዎች ሊያከናውኑት የሚገባቸውን ስራዎች በመለየት እና በሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች አጸድቆ በስራ መዘርዝር ላይ በማካተት ተጠያቂነት በሚያሰፍን ሁኔታ በተጠናከረ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ የታሪፍ ለውጥ ሊደረግባቸው የሚገባቸውን ደንበኞች ለመለየት

የሚያስችለውን አሰራር በመዘረጋት ለተፈጻሚነቱም አስፈላጊው ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

84. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

85. በደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላቱ በናሙና በተደረገ የውስጥ ኦዲት ምርመራ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለንግድ የሚጠቀሙ በርካታ ደንበኞች የፍጆታ ሂሳባቸውን በመኖሪያ ቤት ታሪፍ የሚከፍሉ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. በደንበኛ አገልግሎት መስጫ ማዕከት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለንግድ የሚጠቀሙ በርካታ ደንበኞች የፍጆታ ሂሳባቸውን በመኖሪያ ቤት የታሪፍ ስሌት የሚከፍሉ መሆኑ እንዲሁም በቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎች ላይ የታሪፍ ለውጥ ለማድረግ የሚደረገው አሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ በድህረ ክፍያ ቆጣሪ ላይ የሚደረገው የታሪፍ ለውጥ ራሱን የቻለ ባለሙያ በማዕከላት ደረጃ ባለመኖሩ ምክንያት ስራውን በቆጣሪ አንባቢዎች ላይ ደርቦ የማሰራት ልምድ መኖሩ በናሙና ከታዩ ከሰሜን አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና ቁጥር 5፣ የምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ የደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ የምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ የዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የአዱላላ የደ/አ/መ/ማዕከል እና የቢሾፍቱ ቁጥር-1 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

87. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የታሪፍ ለውጥ በኢንፎርስመንት ቢሮ ከሚሰሩ ተግባራት አንዱ ሲሆን አደረጃጀቱን በተመለከተ በሪጅንና በዲስትሪክት ደረጃ የተዋቀረ የኢንፎርስመንት ቢሮ ለ3 ፌዝና አክቲቭ ሪያክቲቭ ቆጣሪዎች ሲሆን በአገልግሎት መስጫ ማዕከላት በቂ የሰው ሀይል እንዲኖር ጥናት ተሰርቶ የተጠናቀቀ ስለሆነ በቀጣይ የሚሰራ ስራ እንደሆነና በቀጣይ የተቋሙን የፋይናንስ አቅም ከማሳደግ አንጻር ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች የቤት ለቤት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

88. በኦዲቱ በናሙና በታዩት 6 ሪጅኖች ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች key account በመፍጠር የቤት ለቤት አገልግሎት እየሰጡ ያለመሆኑን ፤

89. በኦዲቱ በናሙና ተለይተው መረጃ ከተሰበሰበባቸው 6 ሆቴሎች፤ 8 ባንኮች፣ 4 የምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች፤ 3 የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች እንዲሁም 1 ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በድርጅቱ በኩል ምንም አይነት የቤት ለቤት አገልግሎት እያገኙ አለመሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

90. አገልግሎቱ በሀገሪቷ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገትን የሚያፋጥኑ የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞችን ለይቶ በመመዝገብ ምቹ እና ተደራሽ የሆነ የቤት ለቤት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን አሰራር ስርዓት ተግባራዊ ስለመሆኑ ተከታታይ እና የተጠናከረ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

91. አገልግሎቱ ጉደዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

92. አገልግሎት የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞችን በመለየት ምቹ የሆነ የቤት ለቤት አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑ፤ ከሀይል አቅርቦት ጋር ሚያጋጥማቸውን ችግር በቀላሉ ለመፍታት አዳጋች እንዳደረገው በክትትል ኦዲቱ በናሙና ከታዩ ከራስ ደስታ ሆስፒታል፣ ከማህተመ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ፣ ከሳቢያን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፣ ከጃጉላ ሆስፒታል፣ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ፣ ከአባይ ባንክ ድሬደዋ ቅርንጫፍ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት፣ ከአንበሳ ባንክ ጅግጅጋ ቅርንጫፍ፣ ከቡና ኢንተርናሽናል ባንክ ሀረር ቅርንጫፍ፣ ከንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀረር ቅርንጫፉ፣ ከቃሊቲ ብረታ ብረት

ፋብሪካ፣ ከኮካብ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ድሬደዋ ምግብ ኮምፕሌክስ እና ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች፣ የኢትዮጵያ ሆቴልና ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ - መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

93. አገልግሎቱ ከፍተኛ የሀይል ተጠቃሚዎች (key customer) ደንበኞችን ምቹ የሆነ የቤት ለቤት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘረግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና ቁጥር 5፣ የምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ፣ የሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ የአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ ቁጥር-1 የደንበኞች አገልግሎት ማዕከል እና የጅግጅጋ ሪጅን ደ/አ/መ/ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት ለተለዩ ደንበኞች ፍላጎታቸውን ያገናዘበና የቤት ለቤት አገልግሎትን ጨምሮ ለመስጠት ታስቦ በኮርፖሬት ደረጃ የኢንዱስትሪ ደንበኞች ኃይል አቅርቦት ማስተባበሪያ ቢሮ እንዲሁም በዲስትሪክቶች የኪይ አካውንት ቢሮ ተቋቁሞ እየሰራ እንደሚገኝ፣ በኮርፖሬት ደረጃ የኢንዱስትሪ ደንበኞች ኃይል አቅርቦት ማስተባበሪያ ቢሮ እንዲሁም በዲስትሪክቶች የኪይ አካውንት ቢሮ የተቋቋመው ለተለዩ ደንበኞች ፍላጎታቸውን ያገናዘበና የቤት ለቤት አገልግሎትን ጨምሮ ለመስጠት የታሰበ በመሆኑ ከአዲስ ኃይል አቅርቦት ጀምሮ በአገልግሎት አሰጣጥ ሊደረግላቸው በሚገቡ እገዛዎች ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ፣

95. እንዲሁም በሀረር ሪጅን በሪጅናችን ስር ቁልፍ ደንበኞች ጥቂት /የተወሰኑ/ በመሆናቸው የተነሳ ከፍተኛ ክትትል እና እገዛ ዘወትር እያደረግን እንደሚገኙ፣ በድሬዳዋ ሪጅን ያሉ የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞችን ከ2008/2009 ዓ/ም ጀምሮ የቤት ለቤት አገልግሎት መስጠት መጀመሩን፣ አሁንም በ2011 በጀት ዓመት አገልግሎቱን በማጠናከር የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞችን የቤት ለቤት እና ሰረቬይ ስራ አጠናክረው እየሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

96. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅተ በናሙና በታዩ ከፍተኛ የሀይል ተጠቃሚ ደንበኞች (key customer) የተሰራ ስራ አለመኖሩን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት የቻለ ሲሆን ተሰሩ ስለተባሉ ስራዎችም ለኦዲት ቡድኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>**ክፍያቸውን በአግባቡ በማይፈጽሙ ደንበኞች ላይ**</u>

<u>**ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ፣**</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

76. በአገልግሎቱ ካሉት 15 ሪጅኖች ውስጥ 97 የሚሆኑ የተለያዩ የአገልግሎቱ ደንበኞች ማለትም ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ኤምባሲዎች እና ግለሰቦች ከ1999-2008 በጀት አመት ለተጠቀሙበት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር 80,927,531.81 ለመፈጸም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው በተቋሙ ምንም አይነት እርምጃ እንዳልተወሰደባቸው፣

77. ከዚህ ጋር ተያይዞ የአገልግሎቱን ክፍያን የመሰብሰብ አገልግሎት ከሚሰጠው ከለሁሉ የክፍያ ማዕከል ወደ አገልግሎቱ የሚመጣው መረጃ ደንበኞች ክፍያ ከፍለው እያሉ አልከፈሉም በማለት ሪፖርት የሚደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋረጥ ስራን ከሚሰሩ ባለሙያዎች ጋር አላስፈላጊ ውዝግብ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ እንዳለ፣

78. አገልግሎት መስጫ ማእከላትም ከክፍያ ስርዓቱ ቀጥተኛ ግንኙነት ውጭ/off-line/ የሆኑበት ሁኔታ በመኖሩ የከፈለ እና ያልከፈለን ደንበኛ ለይቶ በማውጣት ሂደት ላይ ችግር እየፈጠረባቸው እንደሆነ በኦዲቱ በናሙና ከታዩት የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከተሰበሰበ መረጃ የታወቀ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

79. አገልግሎቱ ለደንበኞቹ በሰጠው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መሰረት ደንበኞች ክፍያቸውን ሳይፈጽሙ ሲቀሩ ወጥነት ባለው እና በተጠናከረ መልኩ ባስቀመጠው የአሰራር ስርዓት መሰረት ደንበኞቹን በወቅቱ ሊጠይቅ የሚያስችለውን አሰራር ተግባራዊ በማድረግ ይህንን ስራ እንዲፈጽሙ እና ክፍያ ያልፈጸሙ አካላትን በወቅቱ ጉዳዩ ወደ ሚመለከተው አካል መረጃውን ሊያቀርቡ የሚገባቸው የስራ ሃላፊዎች ላይም ተጠያቂነት የሚያሰፍን ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ በማድረግ፣ አገልግሎቱ ከለሁሉ ጋር ያለውን የመረጃ ፍሰት ለቁጥጥር፣ ለክትትል እና ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች

የሚያስችለውን አሰራር ስርዓት ተዘረግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

80. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

81. አገልግሎቱ ለደንበኞች አገልግሎት ሰጥቶ ክፍያውን በወቅቱ በማይፈፅሙ ደንበኞች ላይ ተገቢውን እርምጃ የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን፣ ማዕከሉ ክፍያቸውን በወቅቱ የማይከፍሉ ደንበኞችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲቋረጥ ከተደረገ በኋላ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ ሲሆን አገልግሎት እንዲቋረጥ ከተደረገ በኋላም የማይከፍሉትን ለሰሜን ሪጅን በቃል እንደሚያሳውቁ ከሰሜን አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር-6 የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

82. እንዲሁም ክፍያ በማይፈፅሙ ደንበኞች ላይ በማግባባት እንዲከፍሉ ከማድረግ በስተቀር ሌላ የሚወሰድ እርምጃ አለመኖሩን ከአዱላላና የጅግጅጋ ሪጅን ቁጥር 1 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. አገልግሎቱ ለደንበኞች አገልግሎት ሰጥቶ ክፍያውን በወቅቱ በማይፈፅሙ ደንበኞች ላይ የሀይል አገልግሎት እንዲቋረጥ እንደሚደረግ በናሙና የታዩ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የገለጹ ቢሆንም ሀይል ከማቋረጥ ባለፈ የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ በናሙና ባየናቸው ሁሉም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ማግኘት አልተቻለም፡፡

84. በ2009 በጀት ዓመት የኤሌክትሪክ አገልግሎት በቋሚነትና በግዜያዊነት ከተቋረጠባቸው ደንበኞች ያልተሰበሰበ ውዝፍ የፍጆታ ሂሳብ ብር 84,240,008.25 ቢኖርም አገልግሎቱ ደንበኞቹን በወቅቱ ሊጠይቅ የሚያስችለውን አሰራር ተግባራዊ

ባለማድረጉ የፍጆታ ሂሳቡን መሰብሰብ ያልቻለ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. አገልግሎቱ ደንበኞች የተጠቀሙበትን የሀይል ፍጆታ የክፍያ ሂሳብ እንዲሰበስብለት ውክልና የሰጠው ለሁሉም የክፍያዎች አገልግሎት ተቋም የሚሰጠው አገልግሎት ተደራሽና ቀልጣፋ ባለመሆኑ ምክንያት ደንበኞች ክፍያ ለመክፍል ከለሊቱ 12፤00 ሰዓት ጀምሮ ለረጅም ሰዓታት በመሰለፉ በብርድና በፀሀይ እየተመቱ ክፍያ እንደሚፈጽሙ፣

86. እንዲሁም በሲስተም መቋረጥ ምክንያት ክፍያ ባልፈፀሙ ደንበኞች ላይ የአገልግሎቱ ሰራተኞች ኤሌክትሪክ ለማቋረጥ በደንበኞች ቤት በሚሄዱበት ወቅት ስራውን ከሚሰሩ የአገልግሎቱ ባለሙያዎች ጋር አላስፈላጊ ውዝግብ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

87. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት ከለሁሉ የክፍያ ማዕከል ጋር በተያያዘ ያሉ የመረጃ ልውውጦች በተቻለ መጠን ወቅታዊ እንዲሆኑ እየተሰራ እንደሆነና በቀጣይ ከኢአርፒ ሲስተም ትግበራ ጋር በተያያዘ የገንዘብ ስብሰባው በራሳችን ስለሚሰራ እነዚህ ችግሮች የሚቀረፉ እንደሚሆን፣ የተጠቀሙበትን የፍጆታ ሂሳብ በማይከፍሉ ደንበኞች ላይ ክትትል በማድረግ እንዲከፍሉ እየተደረገ ሲሆን ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑት በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ለማድረግ እየተሰራ እንደሚገኝ፣

88. በአዲስ አበባ ሪጅን አገልግሎት በጊዜያዊነት እና በቋሚነት አገልግሎት ከተቋረጠባቸው ደንበኞች ያልተሰበሰበውን ውዝፍ ሂሳብ በተመለከተ ልዩ ምክንያት ያለባቸውና ለመሰብሰብ አዳጋች የሆኑ ለምሳሌ በልማት ምክንያት የተነሱ እና ባለቤት ለማስቀመጥ ከሚቸገሩባቸው ቆጣሪዎች ውጪ ያሉትን እንደ ተቋም በዘመቻ መልክ በማከናወነን ለመቀነስ ጥረት መደረጉን፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ከነበረው የፀጥታ ችግር አንፃር በስፋት ቆረጣ ቅጠላ የማይካሄድ እንደነበር እና በአሁኑ ወቀት ከክልል መስተዳድሮች ጋር በመሆን የማይከፍሉ ደንበኞች ቆረጣ ቅጠላ በማድረግ ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ላይ እንደሚገኙ፣

89. በተቋሙ አሰራር መሰረት በወቅቱ ክፍያ የማይፈጽሙ ደንበኞች ላይ አገልግሎት በጊዜያዊነት ተቋርጦ ክፍያ እንዲፈጽሙ እንደሚደረግ፣ ይህን ያላደረጉ ደንበኞች በህግ የሚጠየቁበት አሰራር ገልጸዋል፡፡

90. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ ሰርተናል ባሉት ስራዎች ላይ የተሰራ ስራ ስለመኖሩ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለመመልከት ያልተቻለ ሲሆን ስራው መሰራቱን የሚሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ባለመቅረቡ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>የኃይል ብክነት ለመቆጣጠር የተዘረጋው ስርዓትን በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

91. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 6 ሪጅኖች እና 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን ውጪ ቀሪዎቹ ሪጅኖች እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የኃይል ብክነት የቁጥጥር ስራ ስለመስራቱ የሚያሳይ መረጃ በኦዲቱ ወቅት ያላቀረቡ መሆኑ፣

92. የተቋሙ የኃይል ስርቆት እና የትርፍ ኃይል ጭነት ኢንስፔክሽን ስራ አፈጻጸም ሪፖርት ግልጽነት የጎደለው መሆኑ ለአብነትም ተቋሙ በ2008 በጀት ዓመት በ34,202 ደንበኞች ላይ የሃይል ስርቆትን የመከላከል ኢንስፔክሽን ስራ ለመስራት ያቀደ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ምን ያህል ደንበኞች ላይ የኢንስፔክሽን ስራ እንደሰራ ሳይገለጽ በድፍኑ 351 ስርቆቶችን መዝግቦ ብር 8,378,940 ገቢ ያገኘ እንደሆነ ሪፖርት መቅረቡ፣

93. በተመሳሳይ ሁኔታ በተጠቀሰው በጀት ዓመት 34202 ያልተፈቀደ የኃይል ጭነት የመከታተል ስራ ለመስራት ታቅዶ በምን ያህል ደንበኞች ላይ የኢንስፔክሽን ስራ እንደተሰራ ሳይገለጽ በድፍኑ 508 የሚሆኑ ደንበኞች ያልተፈቀደላቸውን ኃይል ሲጠቀሙ ማግኘቱን ሪፖርት ያደረገ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

94. አገልግሎቱ በደንበኞች እየተፈጸመ ያለውን ውስብስብ የኃይል ብክነት እና የትርፍ ኃይል ጭነትን ውጤታማ በሆነ እና በተጠናከረ መልኩ ለመከላከል የሚያስችለውን በስራ ማስኬጃ ግብዓት /ሎጅስቲክ ፣በእውቀት የተደራጀ የሰው ኃይል፣ስራውን ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ሊያሰራ በሚችል አደረጃጀት እራሱን በማደራጀት ተጠያቂነት

የሚያሰፍንና ውጤታማ የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

95. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

96. አገልግሎቱ በ 2009 ዓ.ም 1,140,072 የቆጣሪ ምርመራ ስራ ለመስራት አቅዶ 174,558 በመስራት የእቅዱን 15.3% ማከናወኑን፣

97. በአገልግሎቱ የተጠናከረ የኢንስፔክሽን ስራ የማይሰራና ቆጣሪ አንባቢዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡ በመሆኑ ምክንያት ከቆጣሪ በፊት የኤሌክትሪክ ስርቆት የሚፈጽሙ ደንበኞች መበራከታቸው፣ እንዲሁም በ2010 ዓ.ም በተለያዩ ማዕከላት የሚገኙ የቅድመ ክፍያ ቆጣሪዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የኢንስፔክሽን ስራ ባለመሰራቱ ምክንያት የቁጥጥር ስርዓቱን ደካማ ያደረገ መሆኑ፣

98. አገልግሎቱ በደንበኞች የሚፈፀመውን ያልተፈቀደ የሀይል አጠቃቀም/ የሀይል ብክነት/ ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በማዕከል ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉንና ይህን የሚከታተል የሰው ሀይል የሌለ መሆኑን የሰሜን አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር-6 የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

99. አገልግሎቱ በደንበኞች የሚፈፀመውን ያልተፈቀደ የሀይል አጠቃቀም/ የሀይል ብክነት/ ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በማዕከል ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን፣ ነገር ግን በድህረ ክፍያ ቆጣሪዎች ላይ ቆጣሪ አንባቢዎች በሚያነቡበት ወቅት የማረጋገጥ ስራ እንደሚሰሩ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. አገልግሎቱ በደንበኞች የሚፈፀመውን ያልተፈቀደ የሀይል አጠቃቀም የሀይል ብክነት መኖሩን ለመቆጣጠር በእቅድ ይዘው እንደማይሰሩ ነገር ግን የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ቢል በማየትና የቢል መጠኑም ከዚህ ቀደም ከሚከፈለው የተለየ ከሆነ የሀይል

ብክነት መኖሩን እንደሚያውቁ በተጨማሪም ከአንባቢው ወይም ከደንበኞች በሚመጣ ጥቆማ መሆኑን የዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 እና የገላን የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

101. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በኦሮሚያ ሪጅን በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት የሪጅኑ አውቶሜሽን የምርመራ ስራን አጠናክሮ እየሰራ የሚገኝ በመሆኑ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ እንዳገኘ፣ በ2008 በጀት ዓመት 277,243 ቆጣሪ መመርመሩን፣ ከቆጣሪ ምርመራና ተያያዥ ስራዎች ጋር በተያያዘ ትኩረት በመስጠት ለመስራት ጥረት እየተደረገ ሲሆን ከአደረጃጀት ጋር በተያያዘ ከማዕከል ጀምሮ እስከ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በመፈተሽ በአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የኢንስፔክሽን ባለሙያዎችን እንዲመደቡ እንደተደረገና ወደፊት በዕቅድ ተደግፎ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

102. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ ሰርተናል ባሉት ስራዎች ላይ የተሰራ ስራ ስለመኖሩ ለኦዲት ቡድኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ስርዓት ስለመዘርጋቱ በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

103. በናሙና ከታዩ 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የቅሬታ መቀበያ ፎርም ከማዕከል ማዕከል እንደሚለያይና አንድ ወጥ የሆነ የቅሬታ መቀበያ ፎርም የሌለ መሆኑን፣

104. የአገልግሎት መስጫ ማዕከላቱም በተጠናከረ መልኩ የደንበኞች ቅሬታን በማይሰበስቡበት ፤ የቀረበው ቅሬታ ስለመፈታቱ የሚያሳይ መረጃ በሌለበት ሁኔታ በየወሩ ለሪጅን ቅሬታ (ግሪቫንስ) ቢሮ ከደንበኞች የተነሳ እና የተፈታ ቅሬታ ሪፖርት አዘጋጅተው የሚልኩበት ሁኔታ መኖሩን፣

105. የተገልጋዮች ቅሬታ ወይም ጥቆማ የሚያቀርቡበትና ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ በሪጅንም ሆነ በአገልግሎት መስጫ ማዕከላት በበቂ ሁኔታ ባለመደራጀቱ የተነሳ ዋናው መ/ቤት የሚደርሱ ቅሬታዎች መኖሩ እንዲሁም ተቋሙ የደንበኞች ቅሬታ መቀበያ ስርዓትን ደንበኞቹ እንዲያውቁት ለማድረግ በቂ ስራ ያልተሰራ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

106. አገልግሎቱ የቅሬታ አፈታት ስርዓትን ተፈጻሚ ለማድረግ እንዲያስችለው ከደንበኞች የሚነሳውን ቅሬታ በአግባቡ እና በወቅቱ ስለመፈታቱ ለመከታተል፣ተጠያቂውን አካል ለመለየት፣ከማዕከላት በየወሩ የሚላከውን የደንበኞች ቅሬታ ሪፖርት ታዕማኝነት ያለው ስለመሆኑ በመረጃ ለማስደገፍ የሚያስችል እና የደንበኞቹን እርካታ ለመጨመር የሚያስችል የሚመለከታቸውን የውስጥ እና ውጪ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ የደንበኞች ቅሬታ ማቅረቢያ ቅፅ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

107. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

108. በ2009 ዓ.ም በደንበኞች አገልግሎት ማዕከል ከቀረቡት 190,025 ቅሬታዎች ውስጥ በወቅቱ ለ 116,788 ምለሽ በመስጠት አፈፃፀሙ 61.5 በመቶ መሆኑን፣

109. አገልግሎቱ ከደንበኞች የሚነሱትን ቅሬታዎች ለመፍታት በሚያስችል መልኩ ቅሬታዎችን የሚፈታበት ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን፣

110. ደንበኞች አገልግሎት በሚፈጉበት ወቅት በስልክም ሆነ በአካል የሚያሳውቁበት እና ተራ ለማስያዝ የሚመዘገብበት አሰራር ቢኖርም ፈጣን ምላሽ የሚሰጥበት ስርዓት የሌለ መሆኑን የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት፣ የድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፍብሪካ፣ ከኮኮብ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ከቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣ ከራስ ደስታ ሆስፒታል፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ከማህተመ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ የኢትዮጵያ ሆቴል እና ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

111. ከደንበኞች በየግዜው የሚነሳውን የሀይል አቅርቦት፣ የትራንስፎርመርና የቆጣሪ ጥያቄዎች ደ/አ/መ/ማዕከሉ ካለው የእቃና ተያያዥ ግብዓቶች በላይ በመሆናቸውና የአቅርቦት ችግር በመኖሩ ለዲስትሪክት ከማሳወቅ ባለፈ የደንበኛውን ቅሬታዎች

የሚፈቱበት አሰራር ያለመኖሩን በናሙና ከታዩ ሁሉም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

112. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት ከክትትል ኦዲተ በኋላ በኮርፖሬት በተሰጠው አዲስ ቅሬታ መቀበያ መመሪያ መሰረት ወጥ በሆነ መልኩ እየተሰራ እንደሚገኝ፣ የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ወጥ በሆነ መልኩ እንዲተገበር የቅሬታ አፈታት ፕሮሲጀር ተዘጋጅቶ ለሁሉም ሪጅኖች መላኩንና ደንበኞችም በቂ መረጃ ኖሯቸው ጥያቄያቸውን ማቅረብ እንዲችሉ ስለአሰራር መመሪያው ግንዛቤ እንዲኖራቸው መረጃ የሚሰጥ እንደሚሆን፣ በነበረው የግብዓት አቅርቦት እጥረት ምክንያት ከኃይል አቅርቦት አንጻር የሚመጡ ቅሬታዎችን መመለስ ካለመቻል ጋር በተያያዘ ሁሉንም ቅሬታዎች ለመመለስ አስቸጋሪ በመሆኑ አፈጻጸሙ 100 ፐርሰንት ሊሆን የማይችልበት ሁኔታ መኖሩን፣

113. የተቋሙ ቁልፍ ደንበኞች ሃይል በሚቋረጥባቸው ጊዜ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ ተመልሶ እንዲገናኝ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን፣ ከዲስትሪብዩሽን ግብዓቶች አቅርቦት አንጻር ከሃገር ውስጥ አምራቾች ጋር በተገባ ውል መሰረት ዕቃዎቹ እየቀረቡ በመሆኑ በዚህ በጀት ዓመት ሁሉንም ደንበኞች በማገናኘት ከፍለው አገልግሎቱን ካለማግኘት ጋር የሚነሱ ቅሬታዎችን ለማስቀረት እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የደንበኞች መብትና ግዴታን በተመለከተ አሰራሮች ሲሻሻሉ ድርጅቱ ለደንበኞቹ የሚያሳውቅ መሆኑን በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

114. በኦዲቱ በናሙና ከተለዩት 29 የተቋሙ ደንበኞች መረጃ ከሰጡት ሃያ ሁለት ተቋማት (6 ሆቴሎች፣8 ባንኮች፣ 4 የምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች፣ 3 የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች እና አንድ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) በጠቅላላው ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች በድርጅቱ በኩል የደንበኞች መብትና ግዴታን በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ እንዳልደረሳቸው በመስክ ምልከታ ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ መቻሉ፣

115. በኦዲት ስራው ወቅት የኦዲት ቡድኑ በአካል ተዘዋወሮ የተመለከታቸው ከምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን ውጪ የተቀሩት 5 ሪጅኖች እና 15 ዲስትሪክቶች ስለሚሰጡት አገልግሎት፣ስለ ደንበኞች መብትና ግዴታ፣ስለ የኃይል ስርቆትን መከላከል

ማስተማሪያ የሚሆኑ ብሮሸሮች እና ፓፕሌቶች እና ሌሎች መረጃ የማስተላለፊያ መንገዶች በማዘጋጀት ለደንበኞቻቸው ተደራሽ እንዲሆን ያላደረጉ መሆኑ በኦዲቱ ተገኝቶ ነበር፡፡

116. አገልግሎቱ በሚሰጠው ወቅታዊ አገልግሎት ዙሪያ የደንበኞች መብትና ግዴታምን እንደሆነ የሚያስገነዝብ በቂ እና ተደራሽነት ያለው የመረጃ ማሰራጫ ዘዴ በመጠቀም የደንበኞቹን መረጃ የማግኘት መብት ሊያረጋግጥ የሚችልበትን ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

117. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

118. አገልግሎቱ አሰራሮች ሲቀየሩ ወይም ሲሻሻሉ የደንበኞችን መብትና ግዴታዎች በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎች በቂ እና ተደራሽነት ባለው የመረጃ ማሰራጫ ዘዴ የማያሰራጭ መሆኑን ነገር ግን ማዕከላቱ በራሳቸው አሰራር በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ መረጃዎችን የሚያሰራጩ መሆኑን ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

119. አገልግሎቱ አሰራሮች ሲቀየሩ ወይም ሲሻሻሉ የደንበኞችን መብትና ግዴታዎች ወቅታዊ መረጃዎች በቂ እና ተደራሽነት ባለው የመረጃ ማሰራጫ ዘዴ የማያሰራጭ መሆኑን በናሙና ከታዩት 5 ፋብሪካዎች፣ 3 ሆስፒታሎች፣ 2 ሆቴሎች የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡

120. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት ደንበኞች ለአዲስ ኃይል አቅርቦት ከማመልከት ጀምሮ አገልግሎት አግኝተው በሚጠቀሙበት ጊዜ ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ በተቋሙ የኮሙኒኬሽን

አማራጮች፣ በበራሪ ፅሁፎች እና ሌሎች አማራጮች እንዲያውቁ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በኮሚኒኬሽን የስራ ሂደት በኩል የተቋሙን አሰራር ፤ የደንበኞችን ግዴታ እና መብት ፤ የተቋሙን ግዴታ እና መብት ፤ የታሪፍ ማሻሻያ መረጃዎችን እና ጠቃሚ መረጃዎችን በፍላየር ፤ በባነር እና ብሮሸሮች ተሰርተው በብዛት ተሰራጭተው እንደሚገኙ፣ ተቋሙ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር ውል በመያዝ በቋሚነት ስለተቋሙ የተለያዩ መረጃዎችን ለደንበኞቹ እያደረሰ እንደሚገኝ፣ በተቋሙ ድረ-ገጽና በተለያዩ የኮሙኒኬሽን ዘዴዎች በመጠቀም ደንበኞች የተሟላና ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የተገልጋዮች እርካታ የዳሰሳ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

121. አገልግሎቱ የ2008 በጀት ዓመት የተቋሙ እቅድ አፈጻጸም ላይ የደንበኞችን እርካታ ደረጃ ለመለካት በግማሽ ዓመት በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት የደንበኞች እርካታ ደረጃ 46 ከመቶ እንደነበር እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ በተከናወነው የተገልጋዮች የዳሰሳ ጥናት መሰረት 60 በመቶ እንደሆነ ተደርጎ ሪፖርት የቀረበ መሆኑ፣

122. እንዲሁም በሐምሌ 8 2008 ዓ.ም. ተቋሙ ከህዝብ ፎረም አባላት ጋር ባደረገው ውይይት ላይ ከ93 የፎረም ስብሰባ ተሳታፊዎች በሰበሰበው መረጃ መሰረት የተገልጋዮች እርካታ 60 ከመቶ ደርሷል ብሎ ሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን፣ የተከናወነውም የደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት ተቋሙ ካሉት 2.46 ሚሊዮን ደንበኞች ውስጥ 1 በመቶ በማይሞሉ በ93 ደንበኞች ብቻ መሆኑ በኦዲቱ ተገኝቶ ነበር፡፡

123. አገልግሎቱ የሚሰጠው አገልግሎት ቀጣይነት ያለው፤ጥራትን እና ቅልጥፍናን ያሟላ እንዲሆን ተቋሙ ያለው የደንበኞች ብዛት እና አይነት ባማከለ መልኩ የደንበኞቹን አስተያየት በመሰብሰብ እና በመተንተን በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዙሪያ የማስተካከያ እና ማሻሻያ እርምጃዎች ለመውሰድ እና የደንበኞቹን እርካታ ለማሳደግ የሚያስችል ወጥነት ባለው መልኩ የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማድረግ የሚያስችለውን ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

124. አገልግሎቱ ጉዳን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

125. በ2009 ዓ.ም የእቅድ አፈፃፀም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የደንበኞችን እርካታ ለመወሰን በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አማካይ የእርካታ ደረጃ 68 በመቶ መሆኑን፣

126. አገልግሎቱ የሚሰጠው አገልግሎት ቀጣይነት ያለው፣ ጥራትን እና ቅልጥፍናን ያሟላ እንዲሆን አገልግሎቱ የተገልጋይን እርካታ በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ያላከናወነ መሆኑን በናሙና ካየናቸው ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከቢሾፍቱ ቁጥር-1 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

127. አገልግሎቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ለህዝቡ ተደራሽ ከማድረግና የሚሰጠውንም ግልጋሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተገልጋይን እርካታ በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ለማከናወን ያልተጠየቁ መሆኑን በናሙና በታዩት 5 ፋብሪካዎች፣ 5 ሆስፒታሎች፣ 2 ሆቴሎች የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

128. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት ደንበኞች ተቋሙ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ያላቸውን የእርካታ ዳሰሳ ለማከናወን የሚያስችል ወጥ የሆነ ስታንዳርድ ለሁሉም ሪጅኖች እንዲደርስ መደረጉን እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ በመመሪያው መሰረት የደንበኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት እንደሚደረግ፣ በተጨማሪም በገለልተኛ አካል የእርካታ ዳሰሳ ጥናት እንዲከናወን የግዢ ሂደት መሆኑን እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናትና ከከፍተኛና መካከለኛ የሃይል ተጠቃሚዎች ጋር የውይይት መድረኮች እንደሚደረጉ ገልጸዋል፡፡

<u>በውስጥ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ድርጅቱ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

129. የአገልግሎቱ የውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል በተለያዩ ማዕከላት እና ሪጅኖች ላይ ከ2006-2008 ዓ.ም. ባሉት በጀት ዓመታት ውስጥ ያከናወናቸው የኦዲት ስራዎች የሚገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ድርጅቱ ወቅታዊና አስተማሪ እርምቶችን ወይም እርምጃዎችን የማይወስድ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

130. አገልግሎቱ በውስጥ ኦዲት ስፊ የሆነ ስራ እየተሰራ ያለበት ሲሆን በተገኙ ግኝቶች ላይ ሪጅንና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የእርምት እርምጃ ሰለመውሰዳቸው ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ተግባራዊ ሊያደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

131. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

132. አገልግሎቱ በ2009 በጀት ዓመት በደቡብ ምስራቅ ሪጅንና አዲስ አበባ ሪጅኖች ከመንግስት ቢሎች ያልተሰበሰበ ውዝፍ የፍጆታ ሂሳብ ብር 66,752,020.41፣ በደንበኞች ግምት ሂሳብ አሰራር ላይ በተፈጠረ ስህተት ብር 6,201,494.68 እና በሌሎች አሰራሮች ምክንያት ብር 969,913.46 በጠቅላላ ድምር ብር 73,923,428.56 ያጣ ቢሆንም በግኝቱ መሰረት እርምጃ በመውሰድ እንዲመለስ አስተያየት ቢሰጥም አገልግሎቱ ለኦዲት ሪፖርቱ ትኩረት ባለመሰጠቱ ማስመለሰ ያልቻለ መሆኑ፣

133. በ2010 ዓ.ም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት ከተሰጡ 515 ብዛት ያላቸው የኦዲት አስተያቶች መካከል 318 ወይም 61.7 % የኦዲት አስተያቶች በአገልግሎቱ ምላሽ ያላገኘ መሆኑ፣

134. አገልግሎቱ በ2009 በጀት ዓመት በአሰራርና አፈጻጸም ፣ በንብረትና በጥሬ ገንዘብ ላይ ባደረገው የውስጥ ኦዲት ብር 56,227,688.96 ብር ግኝት የተገኘ ሲሆን በግኝቱ መሰረት ማሻሻያ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም አገልግሎቱ ትኩረት ባለመስጠቱ በርካታ ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤

135. በ2010 ዓ.ም የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በደቡብ አ.አ ዲስትሪክት የደ/አ/መ/ማዕከል ቁ.5 በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰቡና ከ11 አመታት በላይ የቆዩ ብር 39,534.09 ዋጋ ያላቸው 123 የቀድሞ ቢሎች በተደጋጋሚ በውስጥ ኦዲት ሪፓርት አስተያየት ቢሰጣቸውም ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

136. በአገልግሎቱ በ2010 በጀት ዓመት በውስጥ ኦዲት ሪፖር ከአሰራርና ከአፈጻጸም ችግሮች ምክንያት ብር 49,424,885.8 ጉድለት ሲሆን በኦዲት ግኝት መሰረት እርምጃ በመውሰድ ማስተካከል ያለበት ቢሆንም ብር 451,913.93 ወይም 0.91 ፐርሰንት ብቻ ማስመለሰ የተቻለ መሆኑ፤

137. በአገልግሎቱ በ2010 በጀት ዓመት በውስጥ ኦዲት ሪፖርት ከጥሬ ገንዘብ እምነትና ንብረት ማጉደል ችግሮች ምክንያት ብር 7,810,918.14 ጉድለት የታየበት ሲሆን በግኝቱ መሰረት እርምጃ በመውሰድ ሲገባው ለኦዲት ግኝቱ ትኩረት ባለመስጠቱ ብር 556201.05 ወይም 7.12 ፐርሰንት ብቻ ማስመለሰ የቻለ መሆኑ፣

138. በአገልግሎቱ በ2011 በጀት ዓመት በውስጥ ኦዲት ግኝት መሰረት ከአሰራርና ከአፈጻጸም ችግሮች ምክንያት ብር 73,612,745 ጉድለት ያሳየ ቢሆንም በበላይ አመራር ትኩረት ማነስ ምክንያት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

139. አገልግሎቱ በሚያከናውነው የውስጥ ኦዲት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ ወቅታዊ የሆነ የእርምት እርምጃ እንደሚወስድ የደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ የምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና የዱከም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

140. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በውስጥ ኦዲት በሚቀርቡት ግኝቶች ላይ ማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ስራ አመራር ቦርድ ድረስ ውይይት እየተደረገባቸው እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል

እየተደረገ እንደሚገኝ፣ በተወሰደው እርምጃ ብር 1,490,586.60 ገቢ መሰብሰቡን፣ ከአጠቃላይ 515 የኦዲት አስተያየቶች 292 ወይም 57 % የኦዲት አይተያየቶች ላይ የተሰጠ ምላሽ አለመኖሩን፣ በአሰራር ምክንያት ተቋሙ ያልሰበሰበው ሂሳብ በጥሬ ገንዘብና ንብረት ላይ ከተከሰተው አጠቃላይ ብር 3,698,823.88 ውስጥ ብር 722,435.34 ተመላሽ መደረጉን፣ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብ ከአጠቃላይ ጉድለቱ 19.53% ብቻ መሆኑን፣ በ123 የቀድሞ ቢሎች(Old Bills) ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩን፣ ብር 1,228,112.36 መሰብሰቡ የተገለጸ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ መሰብሰብ ከሚገባው 2% ያህሉ ብቻ ነው፡፡

141. በ2010 ዓ.ም ከጥሬ ገንዘብና ከንብረት አጠቃላይ ጉድለት ውስጥ ብር 560,077.05 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ይህም 7.17 ያህሉ መሆኑን፣ ተቋሙ በ2011 በመጀመሪያው ሩብ በጀት አመት በአሰራር ችግር ምክንያት ያጣው አጠቃላይ ገንዘብ ብር 21,426,657.80 ውስጥ ብር 127,015.03 ተመላሽ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

2.2 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮች ብልሽት ቅድመ መከላከልና ድህረ ጥገና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችና የትራንስፎርመሮች ላይ የቅድመ ብልሽት ጥገና ስራዎችን ማከናወኑን በተመለከተ፣

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

142. የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ የተለያዩ ቦታዎች በተንቀሳቀሰበት ወቅት በተለይም ምስራቅ እና ጅጅጋ ሪጅን ከተማ ውስጥ ያሉትም ሆነ በገጠር አካባቢ የሚገኙ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ ምሶሶዎች የተንጋደዱና ሊወድቁ የደረሱ መሆናቸው፣

143. ከ2006-2008 በጀት አመታት በእቅድ እና እቅድ አፈፃፀም ሪፓርት ላይ የመስመርና የትራንስፎርመር ቅድመ መከላከያ ጥገና ስራዎችን ስለመሰራቱ የአፈፃፀም ሪፓርት በቁጥር የተገለፀ ቢሆንም፣ በ6 ሪጅኖች የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ በሄደበት ወቅት ስራው ስለመከናወኑ የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ ተጠይቆ ያላቀረቡ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

144. አገልግሎቱ የ15 ሪጅኖች በጥናት ላይ የተመሰረተ በእቅድ ተይዞና ትኩረት ተሰጥቶ የመስመርና የትራንስፎርመር ቅድመ መከላከያ ጥንቃቄ ስራዎች እንዲሁም የማሻሻያ ስራዎች ሊሰራ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

145. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

146. ትራንስፎርመሮች የደህንነት መጠበቂያና መከላከያ አክሰሰሪዎች የማይገጠምላቸው፣ ወቅታዊ የቅድመ ጥገና የማይደረግላቸው እና ከሚችሉት የኃይል ጭነት በላይ እንዲጭኑ የሚደረጉ መሆናቸውን በኦሮሚያ ሪጅን በአዳማ ዲስትሪክት በ2010 ዓ.ም በተከናወነ የቴክኒካል ኦዲት ሪፖርት ላይ መገለጹ፣

147. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት በተለያዩ ምክንያች በየግዜው የሀይል መቋረጥ የሚያጋጥም በመሆኑ የኃይል በመቆራረጥ በሚኖርበት ወቅት የባንኩ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ለማድረግ በ2016/2017 በጀት ዓመት ብር 2,189,354 እንዲሁም በ 2017/2018 በጀት ዓመት ብር 2,900,574 ብር እንዲሁም አዋሽ ባንክ ድሬደዋ ቅርንጫፍ ከ12/1/2017 እስከ 12/19/2018 በጀት ዓመት ብር 26,172.36 ተጨማሪ ለጀነሬተር ናፍጣ ወጪ ያወጣ መሆኑን፣

148. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትርክት ስር በሚገኙ ቅርንጫፉ ባንኮች በየግዜው የሀይል መቋረጥ እንዲሁም የሀይል መጨመርና መቀነስ ምክንያት በድሬደዋ አብይ ቅርነጫፍ በ2011 ዓ.ም 9 ኮምፒዩተር፣ በ2011 ዓ.ም በደቻቱ ቅርንጫፍ 1 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር፣ 1 ፋክስ ማሽን፣ በ2011 ዓ.ም በልገ ገባ ቅርንጫፍ 1 ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ 1 ኤች ፒ ፕሪንተር ፣ 1 ፋክስ ማሽን እና በጃጃ ቅርንጫፍ 1 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር፣ 1 ኮይሴራ ፕሪንተር የተቃጠለ መሆኑን ቅርንጫፉ ባንኮቹ ለዲስትሪክት ባንኩ በጻፉት ደብዳቤ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፤

149. አዋሽ ባንክ ድሬደዋ ቅርንጫፍ በቀን 18/03/2011 በሀይል መጨመር ምክንያት 6 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር፣ 1 ዋና ሰርቨር፣ 1 ኤች ፒ ፕሪንተር፣ 1 የኤሌክትሪክ ካኩሌተር፣ 1 ፋና ቴሌቪዥን እና ሱፐር ማክስ ሪሲቨር(Super Max Reciver)

የተቃጠለ መሆኑን ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ድሬደዋ ዲስትሪክት በቀን 19/03/2011 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ ለማወቅ መቻሉ፤

150. የድሬደዋ ምግብ ኮምፕሌክስ አክሲዮን ማህበር በተደጋጋሚ ግዜ የሀይል መቆራረጥ በመድረሱ ምክንያት በማምረቻ መሳሪያዎችና በምርት ላይ የብዙ ሚሊዮን ብር ኪሳራ እያደረሰ በመሆኑ ችግሩን እንዲቀረፍ በተደጋጋሚ ግዜ አገልግሎቱን ቢጠይቁም ምላሽ ባለማግኘታቸው የሀይል መቆራረጡ በከፋ ሁኔታ በመቀጠሉ፡-

- ከቀን 20-28/02/2017 እ.ኤ.አ ባለው ግዜ ውስጥ በዳቦ፣በፓስታና በመኮረኒ ምርት ላይ ብር 6,306,573፣
- ከቀን 02-29/03/2017 እ.ኤ.አ ባለው ግዜ ውስጥ በዳቦ፣በፓስታና በመኮረኒ ምርት ላይ በጠቅላላው ብር 10,118,610፣
- በቀን 7/12/2017 እ.ኤ.አ ባለው ግዜ ውስጥ 200 ኩንታል የፓስታ እና 185 ኩንታል የመኮረኒ ምርት ክራክ በማድረጉና ኪሳራ የደረሰ መሆኑን፣
- እንደ ቅደም ተከተላቸው በቀን 30/06/2009 ዓ.ም በቁጥር 01/ወ14/29775/5 ፣ በቀን 26/07/2009 ዓ.ም በቁጥር 01/መ15/32/5 እና በቀን 16/09/2009 ዓ.ም በቁጥር 01/መ15/574/5 ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ድሬደዋ ሪጅን በጻፉት ደብዳቤ ለማወቅ መቻሉ፤

ምስል 2. የድሬደዋ ምግብ ኮምፕሌክስ አክሲዮን ማህበር በምርት ላይ እያለ በመብራት መቆራረት ምክንያት የተበላሸ ዳቦና ብስኩት በመጋዘን የሚገኝ

151. በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን 53 ትራንስፎርመሮች መከላከያ ቦክስ የሌለው መሆኑ፣ በቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 27 ትራንስፎርመር እና በሰሜን ምዕራብ በጭልጋ ደ/አ/መ/ማዕከል 5 ትራንስፎርመሮች ድሮፕ አውት ፊውዝና አርስቴር የሌላቸው መሆኑ፣

152. በተለያዩ አካባቢዎች የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ሳይገጠምላቸው አገልግሎት የሚሰጡ ትራንስፎርመሮችና ቆጣሪዎች በመኖራቸው አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ መሆኑ፣

153. በአማራ ሪጅን የባህርዳር ከተማ፣ የደሴ ዲስትሪክት፣ የደብረ ታቦር ከተማ፣ የማክሰኚት ደ/አ/ማዕከል የዲስትሪቢውሽን መስመር ላይ ለረጅም ግዜ የሪሀብቴሽን ስራ ያልተሰራ በመሆኑ፣ በከተማው የሚገኙ ትራንስፎርመሮች ከሚችሉት አቅም በላይ ሀይል የተጫኑ በመሆኑ፣ በትንስፎርመር ላይ በተደጋጋሚ የሚደርስ አደጋና ብልሽት በየግዜው የከተማዋ የሀይል መቆራረጥ ምክንያት እንደሆነ፣ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

154. የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመር እና የትራንስፎርመር የብልሽት ቅድመ መከላከል ጥገና ስራዎችን የሚሰሩት በዲስትሪክት ደረጃ ሲሆን የደ/አ/መ/ማዕከሉ የሚሰራው የአነስተኛ ሀይል ተጠቃሚዎችን የቅድመ መከላከል ስራ ቢሆንም በማቴሪያል እጥረት ምክንያት የማይሰራበት ሁኔታ መኖሩ የምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ የሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 6 እና ከዱከም የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

155. አገልግሎቱ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመር እና የትራንስፎርመር የብልሽት ቅድመ መከላከል ጥገና ስራዎችን የሚያከናውንበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን ከቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣ ከምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ከኮኮብ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እና ከራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

156. በሰሜን አዲስ አበባ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 5 በ2011 ዓ.ም ኮልፌ ጤና ጣቢያ አከባቢ የኤሌክትሪክ መስመር ከጣሪያ ጋር ተገናኝቶ አንድ ዳቦ ቤት ከነ ንብረቱ ሙሉ ለሙሉ መቃጠሉን፣ በቃጠሎው የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ እንደማያውቁ፣ ለሪጅኑም እንዳላሳወቁ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ማዕከል ቃጠሎው በደረሰበት አከባቢ የኦዲት ቡድኑ ባደረገው ምልከታ 2 የእንጨት ምሰሶዎች አዝመው በኤሌክትሪክ ገመዱ ብቻ ተይዘው

የቆሙ ሲሆን በእንጨት ምእሶሶዎቹ አከባቢ ጉሊት በመሆኑ የተለያዩ ግለሰቦች ከስሩ እንደሚገቢያዩ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይህንኑ የማዕከሉን ሃላፊ በአካል በማምጣት እንዲመለከተው በኦዲት ቡድኑ ቢደረግም የክትትል ሪፖርቱ እስከወጣበት ቀን ድረስ ምንም እርምጃ በማዕከሉ አልተወሰደም፡፡

157. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የግብዓት አቅርቦት እየተሻሻለ የመጣበት ሁኔታ ስላለ በደስትሪብዩሽን ኔተወርክ ላይ የቅድመ ጥገናና የመልሶ ግንባታ ስራዎች የሚሰሩ እንደሚሆን፣ የትራንስፎርመሮች የደህንነት መጠበቂያና መከላከያን በተመለከተ ጉዳዩን አጣርተው በቀጣይ ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስዱ፣ የሀይል መቆራረጥ ችግርን ለመቅረፍ እንደ ሀገር እየተሰራ ባለው የ8ቱ ከተሞች ፕሮጀክት አንዱ የድሬደዋ ከተማ በመሆኑ በዚህ ፕሮጀክት በተሰሩ ስራዎች የሀይል መቆራረጡን በከፍተኛ ሁኔታ እንደቀነሰው ፣

158. እንዲሁም በሀይል መጨመርና መቀነስ ምክንያት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በአዋሽ ባንክ ላይ የተከሰተውን የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች መቃጠልን አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት በቦታው ሄደው ባጣሩት መሰረት ችግሩ የተፈጠረው በመኖሪያ ቤት ቆጣሪ በመጠቀማቸው በመጠቀማቸው እና ከአቅም በላይ የሆኑ መሳሪያዎችን በመጠቀም የተከሰተ ችግር መሆኑን እና ችግሩን እንደተቀረፈ የገለጹ ሲሆን በድሬደዋ ምግብ ኮምፕሌክስ የኤሌክትሪክ ሀይል በሚቋረጥበት ወቅት ተጠባባቂ ጀነሬተር ባለመዘጋጀቱና ቅድመ ጥንቃቄ (ዝግጅት) ባለማድረጉ የተከሰተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

159. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በአዋሽ ባንክ ላይ የተከሰተውን የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች መቃጠልን አስመልክቶ አገልግሎቱ ለባንኮቹ ምላሽ የሰጠበት ማስረጃ ማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ፣ በድሬደዋ ምግብ ኮምፕሌክስ ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ ሀይል በሚያቋርጥበት ወቅት የማሳወቅ ሀላፊነት ያለበት በመሆኑና አንድ ድርጅት ተጨማሪ ወጪ በማውጣት ጀነሬተር ገዝቶ የማስቀመጥ ግዴታ ያለበት ባለመሆኑ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

ምስል 3. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ባያቸው በደቡብና በምስራቅ አዲስ አበባ አካባቢ የሚገኙ ትራንስፎርመሮች የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ሳይገጠምላቸው አገልሎት እየሰጡ የሚገኙ

የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች ላይ የማሻሻያ ስራ መሰራቱን በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

160. በ15 ሪጅኖች ያሉት የማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸውን ጠብቆ በእቅድ ላይ የተመሰረተ የማሻሻያ ስራዎች ያልተሰራ መሆኑ፣

161. በ15 ሪጅኖች ያሉት የማከፋፈያ ጣቢያዎች ከደንበኞች ፍላጎት ጋር በተናበበ ሁኔታ አስቀድመው እንዲሻሻሉ አለመደረጉ፣

162. በአገልግሎቱ ስር ካሉት ትራንስፎርመሮች ውስጥ 40% ያህሉ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች (አሬስተር እና ድሮፕ አውት ፊውዝ) ባለመኖሩ ምክንያት በ2007 በጀት አመት 1029 ትራንስፎርመሮች በጭነት ምክንያት የተቃጠሉ መሆኑ፣

163. በተጨማሪም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 29 የተቋሙ ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች ኃይል በመቆራረጡ ምክንያት የሚሰጡትን አገልግሎት እንዳይቋረጥ በጄነሬተር ስራው እንዲቀጥል የሚያደረጉ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

164. አገልግሎቱ የ15 ሪጅኖች በጥናት ላይ የተመሰረተ በእቅድ ተይዞና ትኩረት ተስጥቶ የመስመርና የትራንስፎርመር ቅድመ መከላከያ ጥንቃቄ ስራዎች እንዲሁም የማሻሻያ ስራዎች ሊሰራ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

165. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

166. አገልግሎቱ ትራንስፎርመር ማሻሻያ እንዲደረግላቸው ለሚጠይቁ ደንበኞች የትራንስፎርመር እጥረት ምክንያት በ3 ወር ግዜ ውስጥ የትራንስፎርመር ማሻሻያ እንደማይደረግ ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-5 እና 6 ፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር- 9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከቢሾፍቱ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር-1 እና የድሬደዋ ሪጅን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

167. እንዲሁም አገልግሎቱ የማከፋፈያ መስመሮች እና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸውን ጠብቆ የማሻሻያ ስራዎችን በዕቅድ ይዞ እንደማይሰራ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ከቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣ ከምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ከኮከብ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ከማህተመ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ከኢትዮጵያ ሆቴል እና ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

168. አገልግሎቱ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመር እና የትራንስፎርመር የብልሽት ቅድመ መከላከል ጥገና ስራዎችን የሚያከናውንበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል እና ከቢሾፍቱ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

169. አገልግሎቱ በ2009 ዓ.ም የዝቅተኛና መካከለኛ መስመሮች የመልሶ ግንባታ ስራን በተመለከተ 5,744 ኪ.ሜ ለመስራት ታቅዶ 2,177.7 ኪ.ሜ በማከናወን የእቅዱን 38% ማከናወኑ፣

170. መስመሮች አገልግሎት ዘመናቸቸውን ጠብቆ ባለመታደሳቸው፣ በትራንስፎርመር ብልሽትና የኤሌክትሪክ ገመድ ተሸካሚ የእንጨት ምሰሶዎች በምስጥ በመበላታቸውና በመውደቃቸው ምክንያት የሀይል መቆራረጥ በመፈጠሩ ባንኩ ከሚያገኙት ትርፍ በላይ ከፍተኛ ወጪ ለጄነሬተር የሚያወጣ በመሆኑ እና ችግሩን መቅረፍ ባለመቻሉ የባንኩን ህልውና እየተፈታተነ እንደሆነ የመቻሬ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት በጻፉ ደብዳቤ መገለጹ፣

171. በ2009 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም በምስራቅ ሪጅን የሚገኙ የ15 ሺ፣ 33ሺ፣ 45ሺ፣ 66ሺ መካከለኛ መስመሮች በእርጅና እና በመስመሩ ጥራት ችግር በተደጋጋሚ በመውደቁና በመስመር መቆራረጥ ምክንያት የመልካም አስተዳደር ጥያቄ በኤረረ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በጉርሱም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በባቢሌ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ቢሲዲሞ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በኮምቦልቻ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በቀርሳ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በደደር ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በዴሳ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በገለምሶ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ በመቻራ ደ/አ/መ/ማዕከል እና በሚኤሶ ደ/አ/መ/ማዕከል ያስነሳ መሆኑን፣

172. በ2010 ዓ.ም በአገልግሎቱ ውስጥ ከሚገኙ በአማራ ሪጅን የባህርዳር ከተማ፣ የደሴ ዲስትሪክት፣ የደብረ ታቦር ከተማ፣ የማክሰኚት ደ/አ/ማዕከል፣ የወረኢሉ ከተማ፣

በኦሮሚያ ዞን ነጆ ማዕከል፣ በአማራ ሪጅን የደሴ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 2 እና በሱማሌ ሪጅን የአውበሬ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል በከተማው የሚገኙ ትራንስፎርመሮች ከሚችሉት አቅም በላይ ሀይል በመጫኑ፤ የዲስትሪቢውሽን መስመር ላይ ለረጅም ግዜ የሪሀብቴሽን ስራ ያልተሰራ በመሆኑ፣ እንዲሁም በትንስፎርመር ላይ በተደጋጋሚ የሚደርስ አደጋና ብልሽት በየግዜው የከተማዋ የሀይል መቆራረጥ ምክንያት እንደሆነ፣

173. በአማራ ሪጅን በርካታ ማዕከላት ላይ የሀይል ማሻሻያ ያልተደረገላቸው በመሆኑ አዲስ ሀይል ፈላጊ ደንበኞችን ጥያቄ በሚያቀርቡበት ግዜ ማስተናገድ ካለመቻሉም በላይ በየግዜው የከተማዋ የሀይል መቆራረጥ እያስከተለ የሚገኝ መሆኑ፣

174. በሰሜን ሪጅን ለእንደጎባ ደ/አ/መ/ማዕከልና ዓድገብሩ ሳተላይት ጣቢያ፣ የአዲግራት ደ/አ/ማዕከል የዲስትሪቢውሽን፣ የብዘት ደ/አ/ማዕከል ከአድዋ ሰብስቴሽን እስከ ብዘት ዲስትሪክት፣ በሽሬ ዲስትሪክት ከኦክሳድ ጋባ እስከ መከላከያ ካምፕ፣ ከአድዋ ሰብስቴሽን እስከ አክሱም ፣ከአክሱም ከተማ እወደ ስመማ ማዕከል ማና ሳተላይት ጣቢያ፣ ከአድዋ ሰብስቴሽን እስከ ዕዳጋ አርቢ እና ራማ፣ ከሽሬ ሰብስቴሽን ወደ ሰለክለካ ማዕከልና ሳተላይት ጣቢያ፣ ከሽሬ ሰብስቴሽን ወደ ውቅሮማራይ ማዐዕከልና ጭላ ሳተላይ እንዲሁም ከአድዋ ሰብስቴሽን እስከ አደጋ አርቢ ማዕከል ያለው መስመር የመስመር ምሶሶዎች ለረጃም አመታት ማሻሻያ ሳይደረግባቸው በማገልግላቸው ምክንያት ምሶሶዎቹና ሲኒዎቹ እየወደቁ በተደጋጋሚ ደንበኞች የኃይል መቆራረጥ ችግር እያጋጠማቸው መሆኑ በውስጥ ኦዲት ሪፖርት መገለጹ፣

175. በሰሜን ምስራቅ ከቀስታ ሰብስቴሽን ወደ ተንታና በስሩ የሚገኙ ሳተላይት ጣቢያዎች፣ በሰሜን ምስራቅ ከሸዋሮቢት ሰብስቴሽን ወደ አጣዬና ሌሎች ሳተላይት ጣቢያዎች፣ በሰሜን ምስራቅ ከአላማጣ ሰብስቴሽን ወደ ቆቦ ጊራና መስኖ ተጠቃሚዎች እና በምስራቅ ከአሰበ ተፈሪ ሰብስቴሽን ወደ በዴሳ የተዘረጋው የተለያየ መጠን የሀይል ጭነት ያለው የመስመር ምሶሶዎች ለረጃም አመታት ማሻሻያ ሳይደረግባቸው በማገልግላቸው ምክንያት ምሶሶዎቹ እየወደቁ በተደጋጋሚ ደንበኞች የኃይል መቆራረጥ ችግር እያጋጠማቸው እንደሆነ፣ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

176. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በጥናት ላይ የተመሰረተ መልኩ ከፍተኛ የጥናት ስራ ፕሮፖዛል ተሰርቶ /ተቀርፆ/ የሰብስቴሽን ማሰደግ ስራ እንዲሁም ሞባይል ሰብስቴሽኖች እንዲገነብ ለሚመለከታው አካል አቅርበው የማስፈቀድ ስራ /ክትትል/ ላይ እንደሚገኝ፣ በእቅድ ተይዞና ትኩረት ተስጥቶ የመስመርና የትራንስፎርመር ቅድመ መከላከያ ጥንቃቄ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ፣ በተጨማሪም በ6 ከተሞች ፕሮጀክት ውስጥ ሀረር ከተማ አንዷ ሆና የቅድመ ዝግጅት ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ፣ የትራንስፎርመሮችን ብልሽት ለመቀነስ የመከላከያ ዕቃዎች ግዢ ተፈጽሞ ለሪጅኖች መከፋፈሉን፣

177. ተቋሙ የዲስትሪቢዩሽን እቃ አቅርቦት በዋናት ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በነበረ ዉል የሚቀርብ በመሆኑ በሚቀርበዉ እቃ እና በእቅድ ፍላጎት መካከል ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር (ክፍተት) ያጋጥም የነበረ ሲሆን በ2011 በጀት አመት መጀመሪያ ጀምሮ ተቋሙ የሃገር ዉስጥ አምራቾችን በግልጽ ጨረታ በመጋበዝ እና በማወዳደር ዉል ሰጥቶ አቅርቦቱን ሊያሻሽል የሚችል ሰፊ ስራ መስራቱን፣ ከፍለው የሚጠባበቁ ደንበኞችን በተያዘው በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለማስተናገድ እየተሰራ እንደሚገኝ፣

178. አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች በፕሮጀክት መልክ ስራዎችን በመስጠት የመልሶ ግንባታ ስራዎች በመከናወን ላይ እንደሆነ፣ የመልሶ ግንባታው ስራው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያለፈና እንዲሁም ከፍተኛ የአጠቃቀም ሁኔታ ያለባቸው አካባቢዎች ላይ እንደሚሰራ፣ የመልሶ ግንባታው ስራው አፈጻጸም ከግብዓት አቅርቦትና ከፋይናንስ ጋር የሚያያዝ መሆኑን እና የሀይል መቆራረጡን በተመለከተ የምርመራ ስራ በማከናወን የቅድመ መከላከልና የመልሶ ግንባታ ስራዎች ችግሩን ለመቅረፍ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

<u>በከተሞችና በገጠር የኃይል ማሰራጫ መስመር ሲበጠስ የኃይል አቅርቦቱ በተቀመጠው የጊዜ ተመን/ስታንደርድ/ መሰረት እንዲቀጥል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

179. በናሙና ከተወሰዱ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን የኃይል ማሰራጫ መስመር ሲበጠስ በስታንደርዱ መሰረት በ8 ሰዓት ውስጥ ማስተካከያ ተደርጎ

ለደንበኞች አገልግሎት እየተሰጠ ያለመሆኑን፣ እንዲሁም በምስራቅ እና በጅጅጋ ሪጅን የኃይል ማሰራጫ መስመር ሲበጠስ በስታንዳርዱ መሰረት 2 ቀናት ውስጥ ማስተካከያ ተደርጎ ለደንበኞች አገልግሎት እየተሰጠ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

180. አገልግሎቱ ዋየሪ ቢዝነስ አደረጃጀት ደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ድረስ መዋቅሩን አውረዶ በገጠርና በከተማ በኃይል ማሰራጪያ መስመር ሲበጠስ በጊዜ ሰሌዳ (በስታንዳርዱ) መሰረት ለደንበኞች አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

181. አገልግሎቱ ጉዳን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

182. አገልግሎቱ የሀይል ማሰራጫ መስመር ሲበጠስ በ 8 ሰዓታት ውስጥ የማስተካከል ወይም ከመጋቢ መስመሮች በመቀጠል የሀይል አቅርቦት አገልግሎት የመስጠት ስራ እንደሚሰራ የሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-5 እና 6፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል፣ የሀረር ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የጅግጅጋ ቁጥር 1 ደ/አ/መ/ማዕከል እና የድሬደዋ ሪጅን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

183. የሀይል ማሰራጫ መስመር ሲበጠስ ትራንስፎርመሮች ሙሉ በመሆናቸው ከመጋቢ መስመሮች ሀይል የማበዳደር ስራ እንደማይሰሩ ከቢሾፍቱ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር-1 የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

184. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በአንድ ማዕከል የነበረውን የአስቸኳይ ጥገና በማውረድ በሁሉም ማዕከላት የጥገና ማዕከል በማቋቋም የተሻለ አፋጣኝ ምላሽ እየተሰጠ እንደሚገኝ፣ ከአቅም በላይ የጫኑ ሰብስቴሽኖችን በመለየት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በኩል የአዲስ ሰብስቴሽን

ግንባታና የፓወር ትራንስፎርመር ማሻሻያ እንዲደረግ በጋራ እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ያለፕሮግራም የኃይል መቆራረጥን በሚዲያ ቀደም ብሎ ማሳወቅን በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

185. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 29 የድርጅቱ ደንበኞች ያለፕሮግራም የኃይል መቆራረጥ በሚኖረበት ወቅትና መቋረጡም ከ240 ደቂቃ/ 4 ሰዓት/ በላይ የሚቆይ ሲሆን፣ በተቋሙ ኃይል መቼ ተመልሶ እንደሚቀጥል በሬድዮና በቴሌቭዥን እንዲያውቁት የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

186. አገልግሎቱ ያለፕሮግራም የኃይል መቆራረጥ ካለ በተለይም በኃይል መቆራረጥ ከፍተኛ ኪሳራ ለሚደረስባቸው ደንበኞች መቋረጡን ከ240 ደቂቃ/ 4 ሰዓት/ በላይ የሚቆይ ከሆነ በተቋሙ ኃይል መቼ ተመልሶ እንደሚቀጥል በሬድዮና በቴሌብዥን ለተቋረጠው አካባቢ ሊገለፅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

187. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

188. ያለ ፕሮግራም የኃይል መቆራረጥ በሚኖርበት ወቅት መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ በስልክም ሆነ በደብዳቤ የማያሳውቁ መሆኑን በናሙና ከታዩ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ፣ አባይ ባንክ ድሬደዋ ቅርንጫፍ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት፣ የአንበሳ ባንክ ጅግጅጋ ቅርንጫፍ፣ የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ ሀረር ቅርንጫፍ፣ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀረር ቅርንጫፍ፣ ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ድሬደዋ ምግብ ኮምፕሌክስ ፋብሪካ፣ ከምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ ኮከብ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ ፋብሪካዎች፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ከማህተመ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ከራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል፣ ጀጉላ ሆስታል፣ ሳቢያን የመጀመሪያ ሆስፒታል፣ ከኢትዮጵያ ሆቴል እና ኢንተር ኮንትኔታል አዲስ ሆቴል የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

189. አገልግሎቱ ያለ ፕሮግራም የሀይል መቆራረጥ በሚያጋጥመው ወቅት ከ4 ሰዓት (240 ደቂቃ) በላይ የሚቆይ ከሆነ፣ አገልግሎቱ መቼ ተመልሶ እንደሚቀጥል በሬድዮና በቴሌቭዥን ለተቋረጠበት አከባቢ የሚነገርበት አሰራር እንደሌለ እና የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከሎቹም የሀይል መቋረጡን የሚያውቁት በደንበኞች ቅሬታ ሲሆን ማዕከሉም ወደ ዲስትሪክት ደውሎ በመጠየቅ እንደሆነ ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-5 እና 6፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6፣ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል እና ከአዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

190. አገልግሎቱ ያለ ፕሮግራም የሀይል መቆራረጥ በሚያጋጥመው ወቅት ከ4 ሰዓት (240 ደቂቃ) በላይ የሚቆይ ከሆነ፣ አገልግሎቱ መቼ ተመልሶ እንደሚቀጥል በሬድዮና በቴሌቭዥን ለተቋረጠበት አከባቢ የሚነገርበት አሰራር አለመኖሩን፣ በዚህም ምክንያት ለጀነሬተር ከሚያወጡት ወጪ በተጨማሪ ከፍተኛ የሆቴሉ የውጭ ሀገር ደንበኞች /ፕሬዝዳንቶች/ ሊፍት ውስጥ በመብራ መጥፍት ምክንያት እየተያዙ የሀገር ገፅታ እየተበላሸ መሆኑን ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

191. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በብልሽት ምክንያት የተቋረጡ መስመሮች ለሰዓታት በሚቆዩበት ወቅት በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች በመጠቀም ለደንበኞች መረጃ እየተሰጠ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

192. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ ስራዎች ስለመሰራታቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃዎች ለኦዲት ቡድኑ ባመቅረቡ አስተያየቱ ተቀባይነት የለውም ፡፡

<u>**የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ደንበኞችን በተቀመጠው ስታንደርድ ማስተናገዱን በተመለከተ**</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

193. የኦዲት ቡድኑ መረጃ ከሰበሰበባቸው በናሙና ተመርጠው ከታዩ 29 የድርጅቱ ከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች (ማለትም 6 በሆቴል አገልግሎት የተሰማሩ፤8

ባንኮች፣ 4 የምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች፣ 3 የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች እና 1 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ኃይል በሚቋረጥበት ወቅት በስታንደርዱ መሰረት ምላሽ የሚሰጥበት ሁኔታ አለመኖሩን፣ የአስቸኳይ ጊዜ የጥገና ክፍል ስልክ በሠራተኞች ያለመነሳት ችግር እና ደንበኞች በአግባቡ የማይስተናገዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

194. አገልግሎቱ የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ያለበትን የአደረጃጀትና የግብዓት ችግር መፍትሄ በመስጠት ደንበኞች የኃይል መቋረጥ ካመለከቱበት በጊዜ ሰሌዳ (በስታንዳርዱ) መሰረት ለደንበኞች አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

195. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

196. አገልግሎቱ በ 2009 ዓ.ም 5,131,763 የ905 የተነሱ የጥሪ መስተንግዶ ለመስራት አቅዶ 3,244,943 በመስራት የእቅዱን 63.2% ማከናወኑን ከ2009 ዓ.ም የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ መቻሉ፣ የቅድመ ጥገና ሰራ በአግባቡ የማይሰራ በመሆኑና በመስመሮች ላይ ለሚፈጠር ብልሽት አፋጣኝ መፍትሄ የማይሰጥ መሆኑ፣

197. በደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላቱ የአስቸኳይ የጥገና ስራዎች በአግባቡና በፈጣን ሁኔታ ባለመሰራታቸው የሀይል መቋረጥ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በአማካኝ ከ 1- 4 ቀን በላይ ለመጠገን የሚፈጅ መሆኑንና ይህም በደንበኞች ላይ ቅሬታዎች እያሳደሩ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ከዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከደብረ ዘይት ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር1፣ ከገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከሀረር ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ ከሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና 6 ፣ ከምዕራብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ ከደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9 እና ከድሬደዋ ደ/አ/መ/ማዕከል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎችና በመስክ ምልከታ ለማወቅ መቻሉ ፡፡

198. በናሙና በታዩ ሪጅኖች እና በማዕከላት የተዘጋጀው የአስቸኳይ የጥሪ መመዝገቢያ ደረሰኝ ላይ ደንበኛው ያስመዘገበበት ቀን የተቀመጠ ቢሆንም መቼ ጥገናው እንደተሰራ የሚገልጽ የቀን ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ተሰርቷል ብቻ ተብሎ የተቀመጠ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

199. እንዲሁም በጅግጅጋ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁትር 1 እና የአዱላላ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ከደንበኞች የሚቀበልበት የስልክ ጥሪ መመዝገቢያ የደረሰኝ ባለመኖሩ በብጫቂ ነጭ ወረቀት ላይ የሚመዘገብ ሲሆን በመመዝገቢያው ወረቀት ላይ የሀይል መቋረጥ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በአማካኝ በምን ያህል ግዜ ውስጥ አገልግሎት የሰጠ መሆኑን የሚገልጽ የቀን ማስረጃ የሌለው ሲሆን ተሰርቷል ብቻ ተብሎ የተቀመጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

200. አገልግሎቱ ደንበኞች የሀይል መቋረጥ መኖሩን ለአስቸኳይ ጥገና ክፍል ካመለከቱበት ግዜ ጀምሮ በ4 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያደርግ የሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና 6 ፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ቢገልፁም በተባለው ሰዓታት ውስጥ የማይሰራ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በማዕከሉ በመገኘት ከተመለከታቸው የአስቸኳይ ጊዜ የጥገና ማዕከል ፎርሞች ለመረዳት ችሏል፡፡

201. አገልግሎቱ ደንበኞች የሀይል መቋረጥ መኖሩን ለአስቸኳይ ጥገና ክፍል ካመለከቱበት ግዜ ጀምሮ በ4 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደማያደርግና አገልግሎቱም ለደንበኞች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት መሰጠቱን የሚከታተልበት አሰራር አለመኖሩን ከቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ከራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል፣ ከምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት፣ ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፍብሪካ፣ ከኢትዮጵያ ሆቴል እና ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

202. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በሰሜን አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 ፣ በደቡብ አዲስ አበባ ደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9፣ ገላን ደ/አ/መ/ማዕከል፣ ዱከም ደ/አ/መ/ማዕከል እና አዱላላ ደ/አ/መ/ማዕከል የሀይል መቋረጥ በሚኖርበት ግዜ

ከደንበኞች የሚመጡ ቅሬታዎቸውን ለማስተናገድ የሚያስችል የአስቸኳይ ግዜ የጥሪ ማዕከል የሌለው ሲሆን አገልግሎቱን በመደበኛ የስራ ሰዓት በመደበኛ የመስመር ስልክ የሚጠቀም መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

203. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በኢአርፒ ሲስተም አብዛኛው የአገ/መ/ማዕከላት በኔትወርክ የሚገናኝ በመሆኑና በዋናው መ/ቤት የደንበኞች የጥሪ ማዕከል በቅርቡ ስራ ስለሚጀምር ደንበኞች አገልግሎት መቋረጥ ያስመዘገቡበትና አገልግሎቱ ተመልሶ የተገናኘበት ጊዜ ስለሚታወቅ ትክክለኛ መረጃ እንዲኖር እንደሚያደርግ፣ በሲስተም የማይገናኙ ማዕከላት ላይ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንዲኖር እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

<u>የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል በመረጃ ኔትወርክ መተሳሰርን በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

204. በኦዲቱ ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ማዕከል ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል የሚገናኙበት የመረጃ ማስተላለፊያ ስርዓቱ ፈጣንና ቀልጣፋ ባለመሆኑ ጥሪዎቹ ወደ አስቸኳይ ጥገና ማዕከላት መተላለፋቸውንና መስመሩ መስራት አለመሰራቱን ደንበኞች የሚያውቁበት መንገድ የሌለ መሆኑ፣

205. በተጨማሪም ከአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ማእከላት ወደ አስቸኳይ ጥገና ክፍል የሚመጣውን ቅሬታ ምን ያህሉ እንደተፈታና ምን ያህሉ ደግሞ እንዳልተፈታ የሚያሳይ ሪፖርት ሲስተሙ የማያወጣ መሆኑን፣ እንዲሁም በአስቸኳይ ጥገና ስራ በምን መንገድ እየተሰራ መሆኑን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና አመታዊ የተዘጋጀ ሪፓርት አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

206. አገልግሎቱ የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል በመረጃ ኔትወርክ ተሳስረው ደንበኞችም የሚያጋጥሟቸውን የኃይል መቆራረጥ አፈጣኝ መፍትሄ ሊሰጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

207. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ

የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

208. አገልግሎቱ ደንበኞችም የሚያጋጥሟቸውን የኃይል መቆራረጥ አፋጣኝ መፍትሄ ለመስጠት የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ጋር በመረጃ ኔትወርክ ያላስተሳሰረ መሆኑን የጅግጅጋ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የአዱላላ የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የሰሜን አዲስ አበባ ማዕከል የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና 6 ፣ የምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ የደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9 ፣ የምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና የድሬደዋ ሪጅን አገልግሎት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

209. በናሙና ከታዩ በዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ ከአዱላላ የደ/አ/መ/ማዕከል ፣ ሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ በሰሜን አዲስ አበባ ማዕከል የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 6 እና 5፣ በምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ በደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9፣ ከምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና የድሬደዋ ሪጅን አገልግሎት የአስቸኳይ ጊዜ የጥገና ክፍል በሰው ኃይል እና በቁሳቁሶች (ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች) እና የማዕከሉን የስራ ስፋት ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በተሽከርካሪ ያልተሟሉበት ሁኔታ መኖሩን፣

210. ከጥሪ ማዕከላትም ሆነ በአካል ደንበኞች መጥተው የሚያስመዘግቡት ቅሬታዎች የተፈቱ ስለመሆኑ እና ያልተፈቱም ከሆነ ያልተፈቱበት ምክንያት በግልጽና ለተጠያቂነት በሚያመች ሁኔታ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የማይመዘገብ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

211. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በኢአርፒ ሲስተም አብዛኛው የአገ/መ/ማዕከላት በኔትወርክ የሚገናኝ በመሆኑና በዋናው መ/ቤት የደንበኞች የጥሪ ማዕከል በቅርቡ ስራ ስለሚጀምር ደንበኞች አገልግሎት መቋረጥ ያስመዘገቡበትና አገልግሎቱ ተመልሶ የተገናኘበት ጊዜ ስለሚታወቅ ትክክለኛ

መረጃ እንዲኖር እንደሚያደርግ፣ በሲስተም የማይገናኙ ማዕከላት ላይ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንዲኖር እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

ተቋሙ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

212. በአገልግሎቱ የብልሽት ቦታ ጠቋሚ መሳሪያ / fault passage indicator/ ባለመኖሩ በሪጅንና በማዕከላት ያሉት የጥገና ባለሙያዎች አንድ መስመር ላይ ብልሽት በሚያጋጥምበት ወቅት ረዥም መንገድ ተጉዘው ብልሽቱን የሚያገኙበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ ባለሙያዎች ለድካም እንዲሁም ደንበኞች ለቅሬታ እየተዳረጉ መሆኑ፣

213. የጥገና ባለሙያዎች የመስመር ብልሽት በሚያጋጥምበት ወቅት ጥገናውን ለማከናወን እንዲቻል መጥፋት ያለበትን ኃይል እንዲቋረጥ /ከማከፋፈያ ጣቢያ /መልዕክት ለማስተላለፍ የሚጠቅም ዘመናዊ የሬድዮ መገናኛ መሳሪያ/ ያለመኖሩ ስራዎች ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዳይከወን ያደረገ መሆኑ፣

214. አንዱ መስመር ብልሽት በሚያጋጥምበት ወቅት ለደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አማራጭ ያለው የዲስትሪብሽን ሲስተም (Ring system) ባለመኖሩ ደንበኞች በወቅቱ ኃይል እንዳያገኙ የሚያደርግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

215. አገልግሎቱ አሰራሩን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ የደንበኞቹን ፍላጎት ሊያሟላ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ይገባ ነበር፡፡

216. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

217. አገልግሎቱ ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ(የሬድዮ መገናኛ፣የብልሽት ጠቋሚ መሳሪያ (fault

passage indicator) እና ሌሎች ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው መሳሪያዎችን) በመጠቀም ስራዎችን የሚሰራበት አሰራር አለመኖሩን የጅግጅጋ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ ሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የአዱላላ የደ/አ/መ/ማዕከል ፣ የሰሜን አዲስ አበባ ማዕከል የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና 6 ፣ የምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ የደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9፣ የምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና የድሬደዋ ሪጅን አገልግሎት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

218. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት የብልሽት ጠቋሚ ቴክኖሎጂ በሰባት ከተሞች ተግባራዊ መደረጉን፣ የሬዲዮ መገናኛ መሳሪያ ግዢ ተፈጽሞ በስራ ላይ መዋሉን፣ በስምንቱ ከተሞች ፕሮጀክትና በአዲስ አበባ ዲስትሪብዩሽን ሪሃብሊቴሽንና አፕግሬዲንግ ፕሮጀክት የሪንግ ሲስተም እንዲኖር መደረጉን ፣ አብዛኛውን ስራዎችን ቀልጣፋና ዘመናዊ የሚያደርግ የኢአርፒ ሲስተም ትግበራ የመጨረሻ የትግበራ ምዕራፍ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የደንበኞችን ፍላጎት በተሻለ ለማሟላት የሚያግዝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2.3 <u>የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞችን ለማርካት ከውጭ (ከከተማ አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻአካላትጋር በቅንጅት ለመስራት የዘረጋውየአሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማመሆኑን ማረጋገጥ፣</u>

<u>የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ስለመፈራረሙ በተመለከተ</u>

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

219. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከክልሎች ከኢትዮ ቴሌኮም፣ ከክልል መስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት ለመደጋገፍ የመግባቢ ሰነድ ተፈራርመው ስራዎች የሚሰሩበት ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

220. አገልግሎቱ ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚመለከታቸውን የውጭ ባለድርሻ አካላት በመለየት የመግባቢያ ሰነድ በመፈራርም ሰነዱንም ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚገመግምበት ስርዓት ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

221. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

222. አገልግሎቱ ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ከውስጥና ከውጪ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ አለመፈራረሙን የጅግጅጋ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የአዱላላ የደ/አ/መ/ማዕከል ፣ የሰሜን አዲስ አበባ ማዕከል የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና ቁጥር 6፣ የምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ የደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9፣ የምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና የድሬደዋ ሪጅን አገልግሎት የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

223. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የመግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም እየተሰራ እንደሚገኝ እና ለደንበኞች የሚሰጠው አገልግሎት ቀልጣፋና ለማድረግ ከገንዘብ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ከንግድ ባንክ ጋር የመግባቢያ ሰነድ እንደተፈራረሙ ገልጸዋል፡፡

224. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ የመግባቢያ ሰነድ ስለመፈራሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ የኦዲት ቡድኑ ማስረጃ ማግኘት ያልቻለ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከደንበኞች ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ ስለመኖሩ በተመለከተ

በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

225. አገልግሎቱ ከ2006-2007 በጀት አመት ተቋሙ ከደንበኞች ጋር የውይይት መድረክ ያላደረገ መሆኑ፣ በ2008 በጀት አመት ከህዝብ ፎረም ጋር ውይይት ለማድረግ 1437 መድረክ ለማዘጋጀት አቅዶ የተዘጋጀው መድረክ 408 አፈፃፀሙ 28.39% ዝቅተኛ መሆኑ፣ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ 6 ሪጅን የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ውይይት ስለማድረጋቸው የሚያሳይ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

226. አገልግሎቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ከደንበኞች ጋር በተለይም ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች ቋሚ የግንኙነት መድረክ በማዘጋጀት በአገልግሎት አሰጣጡ ያሉትን ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥበት ስርዓት ተግባራዊ ሊያደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

227. አገልግሎቱ ጉዳዩን አስመልክተ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበትን ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡

የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

228. አገልግሎቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ከደንበኞች ጋር ቋሚ የግንኙነት መድረክ አለመዘጋጀቱን የጅግጅጋ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የሀረር የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 1፣ የዱከም የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የቢሾፍቱ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-1፣ የገላን የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የአዱላላ የደ/አ/መ/ማዕከል፣ የሰሜን አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 5 እና 6፣ የምዕራብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 4፣ የደቡብ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር 9 እና የምስራቅ አዲስ አበባ የደ/አ/መ/ማዕከል ቁጥር-6 እና የድሬደዋ ሪጅን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

229. አገልግሎቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ቋሚ የግንኙነት መድረክ ከደንበኞች ጋር አዘጋጅቶ ተጋብዘው እንደማያውቁ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ከራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል፣ ከማህተመ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ በሀረር ከተማ የጀጉላ ሆስፒታል፣ የሳቢያን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፣ ከኢትዮጵያ ሆቴል፣ ከኢንተር ኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል፣

230. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድሬደዋ ዲስትሪክት፣ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ፣ አባይ ባንክ ድሬደዋ ቅርንጫፍ፣ አንበሳ ባንክ ጅግጅጋ ቅርንጫፍ፣ ቡና ባንክ ሀረር ቅርንጫፍ ፣ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀረር ቅርንጫፉ፣ ከቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣ ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፍብሪካ፣ ከምስራቅ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣ ከኮኮብ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ እና የድሬደዋ ምግብ ኮምሌክስ አ.ማ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

231. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት በ2011 በጀት ዓመት ከተደረገው የታሪፍ ለውጥ ጋር በተያያዘ ከከፍተኛና መካከለኛ ኃይል ተጠቃሚዎች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን በቀጣይም በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የምክክር መድረኮች እንደሚደረጉ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከደንበኞች ጋር የግንኙነት መድረኮችን እየተደረገ መሆኑንና በቀጣይ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

232. አገልግሎቱ ይህን ይበል እንጂ የውይይት መድረኮች ስለመዘጋጀቱ እና ተግባራዊ ስለመደረጉ የኦዲት ቡድኑ ማስራጃ ማግኘት ያልቻለ በመሆኑ አስተያየቱን አልተቀበልነውም፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

233. የትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለደምበኞች የሚሰጠው አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ✓ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር የክትትል ኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ግንቦት 02 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 28.3/14/11 አዘጋጅቶ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት መላኩ፣
- ✓ አገልግሎቱ በከተማና በገጠር በኃይል ማሰራጪያ መስመርሲበጠስ በደንበኞች ፓሊሲና ፕሮሲጀር በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ (በስታንዳርዱ) መሰረት መስመሩ ተሰርቶ ለደንበኞች አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ✓ አዲስ የኃይል ፈላጊ ደንበኞች መዝግቦ በመያዝና በከፈሉበት ቀን ቅደም ተከተል መሰረት እንዲስተናገዱ ለማድረግ የመጠባበቂያ ሰንጠረዥ / Waiting List/ የሚለጠፍ መሆኑ፣
- ✓ በየማዕከላቱ የሚገኙ የቆጣሪ አንባቢያን ስራቸውን በአግባቡ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለማከናወናቸው ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል የቆጣሪ አንባቢያን የስራ መመሪያ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀ መሆኑ፣

ናቸው፡፡

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- ✓ አዲስ የኃይል ፈላጊ ደንበኞች መዝግቦ በመያዝና በከፈሉበት ቀን ቅደም ተከተል መሰረት እንዲስተናገዱ ለማድረግ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት ላይ የተጠናከረ ክትትል እና ቁጥጥር የማያደረግ መሆኑ፣
- ✓ በአገልግሎቱ ስር የሚገኙ ሪጅኖች እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በስራቸው ያሉትን ደንበኞች ዝርዝር መረጃ በአግባቡ አደራጅቶና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማይዝ በመሆኑ
- ✓ አገልግሎቱ ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ /ስታንደርድ/ መሰረት ማከናወን አለመቻሉ ደንበኞች እንዲስተጓጎሉ ከማድረጉ በተጨማሪ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት መሆኑ፣
- ✓ በየማዕከላቱ የሚገኙ የቆጣሪ አንባቢያን ስራቸውን በአግባቡ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለማከናወናቸው ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል የቆጣሪ አንባቢያን የስራ መመሪያ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ አለማድረጉ፤
- ✓ አገልግሎቱ የታሪፍ ለውጥ ሊደረግ የሚገባቸውን ደንበኞች ለመለየትና ለመተግበር የሚያስችል አሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ አዲስ የኃይል አገልግሎት ያገኙ ደንበኞችን በሁለት ወር ውስጥ ወደ ክፍያ ስርዓት የሚገቡበት ስርዓት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ ለደንበኞቹ የሰጠውን የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ በማይፈፅሙ የአገልግሎቱ ደንበኞች ላይ አገልግሎት ሀይል ከማቋረጥ ባሻገር ተቋሙ ባስቀመጠው የአሰራር ስርዓት እና የህግ አግባብ የሚጠየቁበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች ምቹ እና ተደራሽ የሆነ የቤት ለቤት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ አለማድረጉ፣

- ✓ አገልግሎቱ በደንበኞች እየተፈጸመ ያለውን ውስብስብ የኃይል ስርቆትን እና የትርፍ ኃይል ጭነትን ውጤታማ በሆነ እና በተጠናከረ መልኩ ለመከላከል የሚያስችል የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ ከደንበኞቹ ለሚነሱት የአገልግሎት አሰጣጥ ቅሬታዎች ቀልጣፋና ተጠያቂነትን ሊያመጣ የሚያስችል በሁሉም ሪጅኖች እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ወጥነት ያለው የቅሬታ መቀበያ ቅጽ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከደንበኞች የሚጠበቅ መብትና ግዴታን በመለየት ለደንበኞቹ ምቹ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ የሚያሳውቅበት ስርዓት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ የደንበኞቹን እርካታ ደረጃ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ያላከናወነ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ በሚያከናውነው የውስጥ ኦዲት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ ወቅታዊ የሆነ የእርምት እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ በእቅድ ይዞና ትኩረት ተሰጥቶ የመስመርና የትራንስፎርመር ቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች ያልተሰራ መሆኑ፣
- ✓ የማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸውን ጠብቆ ካለው ደንበኞች ፍላጎት ጋር በተናበበ ሁኔታ የማሻሻል ስራ ያልሰራ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ ያለፕሮግራም የኃይል መቆራረጥ ካለ መቋረጡን ከ240 ደቂቃ/ 4 ሰዓት/ በላይ የሚቆይ ከሆነ በተቋሙ ኃይል መቼ ተመልሶ እንደሚቀጥል በሬድዮና በቴሌቭዥን ለተቋረጠው አካባቢ የማያሳውቁ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ የአስቸኳይ ጊዜ የጥገና ክፍል ደንበኞችን በሚደውሉበት ወቅት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ምላሽ እያገኙ ያለመሆናቸው፣
- ✓ አገልግሎቱ የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል በመረጃ ኔትወርክ ያልተሳሰረ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ዘመናዊ የሬድዮን መገናኛ፣ የብልሽት ጠቋሚ መሳሪያ እና ሌሎች ከቴክኖሎጂ ጋር ግንኙነት ያላቸውን

መሳሪያዎችን) ባለመጠቀማቸው ለደንበኞች ቀልጣፋአገልግሎት እየሰጡ ያለመሆኑ፣

- ✓ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚመለከታቸውን የውጭ ባለድርሻ አካላት በመለየት የመግባቢያ ሰነድ በመፈራርም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ቋሚ የግንኙነት መድረክ ከደንበኞች ጋር የሌላቸው መሆኑ፣

እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

234. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ጥቂት ብቻ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና የተወሰነ መሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡
ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ እና የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋናው መ/ቤት፣ ዲስትሪክቶች፣ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት እና የተለያዩ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሰራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡